## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በንግድ ሚኒስቴር

## የገቢና ወጪ እቃዎች እና የህጋዊ ስነ-ልክ ደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን በተመለከተ

## የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

አዲስ  አበባ

ማውጫ


**የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)** ........ 4

(EXECUTIVE SUMMARY) ........ 4

**ክፍል አንድ** ........ 6

**መግቢያ** ........ 6

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ........ 7
የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 7
የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች........ 8

**ክፍል ሁለት** ........ 9

**በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች**........ 9

በገቢና ወጪ ዕቃዎች እና ህጋዊ ስነ - ልክ ስራዎች ላይ እስትራቴጂክ ዕቅድና አመታዊ ዕቅድ ያዘጋጀና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ........ 9
ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአሠራር መመሪያ አውጥቶ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ማሳወቁንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋገጠ መሆኑን በተመለከተ፣........ 11
ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በሰው ኃይል እንዲደራጁ በማድረግና ለሥራው የሚሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣ 13
ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ የገቢ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊትና ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ገበያ ላይ ከመዋላቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጡን በተመለከተ፣........ 16
ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ያገደ መሆኑን ፤ ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ፣........ 18
የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳወቁንና ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን፣ ናሙናዎች ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ላብራቶሪ እንዲቀርቡ ማድረጉን በተመለከተ፣ ........ 23
ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የላብራቶሪ ሰርተፊኬት እንዲያቀርቡ ማድረጉንና ፤ የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ያላቀረቡ አስመጪዎች የላብረቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ እንዲጠብቁ ማድረጉን በተመለከተ፣ ........ 26
ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የስነ ልክ ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ቁጥጥር ማድረጉን፣ የመለኪያ መሣሪያዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናክረው መሥራታቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 28

የመለኪያ መሣሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጡን በተመለከተ፣ ..... 35
ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገልጋዮች ቬሪፊኬሽን ለማስደረግ የክብደት ማነፃፀሪያዎች ወስደው እንዳያዘገዩ ውል በማስገባት መሣሪያዎቹ በወቅቱ እንዲመልሱ ማድረጉን በተመለከተ፣ ..... 36
የአውቶ ቦቴ የቬሪፊኬሽን የአገልግሎት ክፍያ ተመን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር መሆኑን ፣ የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር ( ቦቴ) የቬርፊኬሽን ሰርተፊኬት የሚሰጥና ተግባራዊ መደረጉን ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣ ..... 37
ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ፣ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከተገልጋዮች ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ያለው መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 39
ከተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት በየ6 ወሩ ቋሚ የምክክር መድረኮች ያዘጋጀ መሆኑን ፣ ከክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ባለሙያዎች ጋር በየሩብ ዓመቱ ውይይት ማድረጉንና በየስድስት ወሩ ግምገማ ማካሄዱን በተመለከተ፣ ..... 43
ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዘ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይይት ያደረገና መፍትሄ ያስቀመጠ መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 45
ናሙናዎች መረጃ በመረጃ ቋት ተመዝግቦ እንዲያዝ መደረጉን ፣ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለቅ/ጽ/ቤቶችና ለተገልጋዮች እንዲሰራጭ ማድረጉንና ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር መረጃ የሚለዋወጥና መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 47
ሁሉንም የሥራ አመራር ያካተተ መደበኛ እና ተከታታይ የማናጅመንት የውይይት መድረክ ያለው መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 49
በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበር ገምግሞ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን፣ በቅ/ጽ/ቤቶችና በክልሎች በአካል በመገኘት የጋጠሙ ችግሮችን ገምግሞ መፍትሄ የሰጠ መሆኑ በተመለከተ፣ ..... 50
የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያቀርቡትን ወርሀዊ ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን ከገመገመ በኋላ ግብረ መልስ የሰጠ መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 51

ክፍል ሦስት ..... 54

የመደምደሚያ ሀሳብ (CONCLUSION) ..... 54

3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው ..... 54
3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው ..... 55

ክፍል አራት ..... 58

የማሻሻያ ሀሳቦች (RECOMMENDATION) ..... 58

# የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)

## (Executive summary)

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2007/2008 ዓ.ም በንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና የህጋዊ ሥነ-ልክ ደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ፤ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ያከናወነ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት በክትትል ኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው :-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በገቢና ወጪ ዕቃዎች እና በህጋዊ መለኪያ መሳሪያዎች ደረጃ ፍተሻ አፈጻጸም ዕቅድ ክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች በመለየት የመፍትሄ እርምጃ አለመውሰዱ ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የአሠራር መመሪያ ያለማውጣቱ ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያከናውናቸው የደረጃዎች ፍተሻ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን በሥሩ የሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች በተሟላ ሰው ኃይል በማደራጀትና ለሥራው የሚያስፈልጉ አስፈላጊ ግብዓቶችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን እየተከታተለና እየተቆጣጠረ አለመሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ እንዲያግድ በተሰጠው ስልጣን ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች በተስማሚነት ምዘና በላብራቶሪ ፍተሸ ተደርጎላቸው ከደረጃ በታች የሆኑት እንዲታገዱ አለማድረጉን እና መስፈርት የማያሟሉትን በመቆጣጠር ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ አለመውሰዱ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት በተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊ ማድረጋቸው ተገቢውን ቁጥጥር ያላደረገና የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ሥራዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናክረው መስራታቸውን ለማረጋገጥ በቂ የሆነ ስታንዳርድ የመለኪያ መሣሪያዎች የሌሉት መሆኑ ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክልሎች ላይ የሚገኙ የሕጋዊ ሥነ-ልክ ባለሙያዎች የክህሎት ክፍተት ያለባቸውና የሚጠቀሙበት ስታንዳርድ ለመለኪያ መሳሪያዎቹ ለጉዳዩ ትኩረት ካለመስጠትና ከየአቅም ውስንነት አኳያ በየጊዜው ካሊቤሬት የማይደረግና ስራዎቹ መሰራታቸውን የሚከታተልበትና ክፍተቶችና ጥንካሬዎችን የሚከታተልበት አሰራር የሌለው መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ ቬርፊኬሽን ክፍያ በ1966 ዓ.ም የወጣ ሲሆን አሁን ከሚሠጠው አገልግሎትና ወጪ አንጻር ክፍያው ወቅታዊና ተመጣጣኝ ከጊዜው አንጻር እንዲሆን ማሻሻያ ወይም ማስተካከያ ያለመደረጉ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች የሚካሄዱ የህጋዊ ስነ ልክን የስራ አፈጻጸምን በየሩብ ዓመቱ ውይይት ለማድረግና በየስድስት ወሩ ግምገማ ለማድረግ ዕቅድ ቢያዘጋጅም በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ያለማድረጉ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት መዘግየት ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር በመሆን ችግሮችን እንዲቀረፉ ተከታታይነት ያለው ውይይት በማድረግ ለችግሮቹ መፍትሄ እንዲቀመጥ ያለማድረጉ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበርና አሠራርን ላይ ያሉትን ችግሮችን በሰው ኃይል ስልጠና፣ በመሳሪያዎችና ሌሎች አስፈላጊ በሆኑ ድጋፎች በመለየት እየገመገመ በበቂ ሁኔታ ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቅ/ጽ/ቤቶችና በክልሎች በገቢና ወጪ ዕቃዎችና በህጋዊ ስነ ልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሚያቀርቡ ወርሀዊ ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን እየገመገመ ግብረ መልስ የማይሰጥ መሆኑ፣

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ቀድሞ የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ሚኒስቴር በመባል ይታወቅ የነበረው መ/ቤት የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር፣ የውጭ ንግድ ሚኒስቴር፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የቱሪዝም በሚል በ4 መ/ቤቶች ተከፋፍሎ እንዲዋቀር ተደርጎ ነበር፡፡

2. ከዚያም የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር እና የውጭ ንግድ ሚኒስቴር እንደገና በ1983ዓ.ም የንግድ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲዋሃዱ የተደረገ ሲሆን፤በ1987 ዓ.ም ደግሞ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በአዋጅ ቁጥር 4/1987 ዓ.ም በማዋሃድ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንዲደራጅ ተደረጓል፡፡

3. ይህ መ/ቤት በ1994 ዓ.ም 10 ተጠሪ መቤቶችን በስሩ ይዞ እንዲያስተባብር እና እንዲመራ በአዋጅ ቁጥር 256/1994 ተደራጅቶ ነበር ከዚያም እንደገና በአዋጅ ቁጥር 411/1996 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በስሩ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጠሪ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን፣የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ስራዎች ኤጀንሲና የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለእርሱ ተጠሪ ሆነው እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡

4. በአሁኑ ወቅትም የቀጣዮቹን አምስት አመታት መሰረታዊ የዕቅድ አላማዎች፣ የማክሮ ኢኮኖሚ እና የዋና ዋና ዘርፎች ግቦችን፣ የአቅም ግንባታና የመልካም አስተዳደር ተግባሮችን እውን ለማድረግ የፌደራል አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 691/2003 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ በጋራ ሲሰሩ የነበሩ የስራ ዘርፎች በሁለት ሚኒስቴር መቤቶች በተናጥል እንዲደራጁ ተደርጎ የንግድ ሚኒስቴር ተቋቁሟል፡፡

5. በወቅቱም ራሱን ችሎ በሚኒስቴር ደረጃ እንዲደራጅ የተደረገው ቀደም ሲል በግብርናና በገጠር ልማት ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን እና በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲከናወኑ የነበሩ እና ከንግድ ጋር የተያያዙ ተግባራት ወደ አንድ በማምጣት ቀደም ሲል ለሌሎች ተቋማት ተጠሪ የነበሩት የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ

ምርት ገበያንና  የንግድ አሰራር ሸማቾች  ጥበቃ ባለስልጣን ለሚኒስቴር መስርያ ቤቱ ተጠሪ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

**የክትትል ኦዲቱ ዓላማ**

6. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2007/2008 ዓ.ም በንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና የህጋዊ ሥነ-ልክ ደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ፤ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም ዓ.ም. ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ያከናወነ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ነው፡፡

**የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ**

7. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው ከ2008-2010 ዓ.ም ያሉትን የሁለት በጀት ዓመታት እና የ2010 ዓ.ም የግማሽ ዓመት የሥራ ክንውኖችን እንቅስቃሴ መሰረት ባደረገ በንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና የህጋዊ ሥነ-ልክ ደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀም ላይ በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶች/ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ እነዚህን የኦዲት ግኝቶች የሚፈታበት የኦዲት ግኝት ማሻሻያ ሃሳቦች የሚተገበሩበትን የማሻሻያ እርምጃ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ባቀረበው መሰረት የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች በተዘጋጀው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት መተግበራቸውን እና ችግሮቹ መቀረፋቸውን ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲቱ እስከተከናወነበት እስከ 2010 የግማሽ በጀት ዓመት ድረስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተከናወኑ ስራዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

8. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በንግድ ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት እና  በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመረጠው ከታዩ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መካከል የሞጆ ቅ/ፅ/ቤት፣ የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት እና የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት እንዲሁም ሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ፣

አዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣ ሃዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣ እና የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የክትትል ኦዲት ቡድኑ በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለክክትል ኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ነው፡፡

## የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

9. የክትትል ኦዲቱን ለማከናወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

## በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች

**በገቢና ወጪ ዕቃዎች እና ህጋዊ ስነ - ልክ ስራዎች ላይ እስትራቴጂክ ዕቅድና አመታዊ ዕቅድ ያዘጋጀና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

10. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

11. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህጋዊ የስነ-ልክ የሚዛን ልኬት ትክክለኛነት ማረጋገጫ አሠራር ማኑዋል ላይ የሥነ-ልክ ቡድን የትክክለኛነት ማረጋገጫ ሥራ ዓመታዊ ምርመራ እና ድንገተኛ ፍተሻ ሥራ መሠራት እንዳለበት ቢገለጽም በዕቅድ አካቶ የማይሰራ መሆኑ፣ በክልሎች የሚካሄዱ የስነ ልክ ስራዎች የመከታተል የመደገፍ ስራ መስራት ያለበት ሲሆን የስነ ልክ ስራዎችን በእስትራቴጅክ ዕቅድ በማካተት ወደ ክልል በማውረድ ለክልሎች እንዲያውቁት አለመደረጉን፣

12. ክልሎችም የሥነ ልክ ሥራዎችን በተመለከተ ዕቅድ አቅደው የዕቅድ ክንውን ሪፖርታቸውን በየሶስት ወሩ ውክልናው ከተሰጠበት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲልኩ ቢገልጽም በኦዲቱ በናሙና በታዩ የክልል ንግድ ቢሮዎች የአዲስ አበባ ፣ የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ እና የኦሮሚያ ንግድ ገበያ ልማት ቢሮ ውስጥ የኦሮሚያ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ብቻ በየ3 ወሩ የሥነ ልክ ሥራዎችን በተመለከተ ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከ2005-2008 ህዳር መጨረሻ ድረስ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚልክ ሲሆን የአዲስ አበባና የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ዕቅድና አፈጻጸማቸውን እንደማይልኩ ተገኝቶ ነበር፡፡

13. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህጋዊ ሥነ ልክን ቡድን የሚያከናውናቸውን የስነ ልክ ስራዎች ዓመታዊ ምርመራና ድንገተኛ ፍተሸ በእስትራቴጂክ ዕቅዱ አካቶ አመታዊ ዕቅድ እንዲያቅዱ ሊያደርግና እንዲሁም የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት የሚያከናዉኑዋቸውን የህጋዊ ስነ-ልክ ስራዎች መ/ቤቱ በእስትራቴጂክ ዕቅዱ በማካተት ለክልሎች ሊያወርድና ክልሎችም ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በተቀመጠው ጊዜ (በየ3 ወሩ) እንዲያቀርቡ ሊያደርግና አፈጻጸማቸውን ሊገመግም በገቢና ወጪ እቃዎች እና በመለኪያ መሳሪያዎች ደረጃ

ፍተሻ አፈጻጸም ክንውን ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሂ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

14. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ክልሎች የዕቅድ አፈፃፀማቸውን በየሶስት ወሩ እንዲልኩ በማድረግ ስለአፈፃፀማቸው በየስድስት ወሩ ከክልሎች ጋር በመገናኘት ግምገማ ለማከናወንና የሚታዩ ክፍተቶች ላይ የመፍትሂ እርምጃ ለመውሰድ በ2009 ዓ.ም በጀት ዓመት እቅድ ላይ አካቶ ተግባራዊ ለማድረግ መታቀዱን እና እንዲሁም ዓመታዊና ድንገተኛ የነዳጅ ሜትሮች ምርመራ ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ለማከናወን በ2009 በጀት ዓመት እቅድ ውስጥ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

15. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

16. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና በህጋዊ የመለኪያ መሳሪያዎች ደረጃ ፍተሻ እስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ስትራቴጂክ ዕቅዱን መሰረት አድረጎ አመታዊ ዕቅድ እና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የእቅድ ክንውን ሪፖርት የሚያዘጋጅ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

17. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በእቅድ አፈፃፀም ክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች በመለየት የመፍትሂ እርምጃ እየወሰደ እንደሚገኝ የሞጆ እና የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች የገለፁ ሲሆን የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ሃላፊ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጪ ዕቃዎች እና በህጋዊ መለኪያ መሳሪያዎች ደረጃ ፍተሻ አፈጻጸም ዕቅድ ክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ እንደማይወስድ ገልፀዋል፡፡

18. በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በ 2009 ዓ.ም 1200 ሜ.ቶ የጥጥ ፈትል በመፈተሽ ወደ ውጪ እንዲወጡ ለማድረግ ታቅዶ 223.4 ሜ.ቶ ወይም 18.6% የኢንስፔክሽን ስራን በማከናወን ወደ ውጪ እንዲወጡ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑን ከአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የ 2009 በጀት ዓመት ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

19. አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የወጪና የገቢ ምርቶች እና አስገዳጅ ደረጃ የሌላቸው የገቢ ምርቶች ጥራት በመጓደሉ የሸማቹ ህብረተሰብ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት ማስከተሉና የንግድ ውድድር ሥርዓቱ ማዛባቱ እንዲሁም ሀገሪቱ በምታከናውናቸው በማህበራዊና ኢኮኖያዊ መሰረተ ልማት ግንባታዎች ላይ አሉታዊ

ተፅኖ መፍጠሩን ከንግድ ሚኒስቴር የ2009 ዓ.ም እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

20. ወርሃዊ ሪፖርትን በተመለከተ የሞጆ ቅ/ፅ/ቤት ወርሃዊ ፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት እና ኣመታዊ እቅድ በማቀድ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት እንደሚያደርጉ ፣ የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት ለሚ/ር መ/ቤቱ እቅድና የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በየስድስት ወሩ የሚልኩ መሆኑን ፣ የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት እቅድ በማቀድ በየወሩ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚልኩ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ታውቋል፡፡

21. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በገቢና ወጪ ዕቃወች ጥራት ቁጥጥር ከቅ/ጽ/ቤቶች ጋር በየሩብ ዓመቱ መደበኛና ቋሚ ስብሰባ ያለዉ መሆኑን እና በእቅድ አፈጻጸምና በአሰራር ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ዙሪያ ግምገማና ዉይይት በማድረግ ግብረ መልስ የሚሰጥ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

22. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን ይበል እንጂ በክትትል ኦዲት ቡድኑ በናሙና በታዩ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶችም ሆነ በዋናው መ/ቤት በገቢና ወጪ እቃዎች በአሰራር የሚታዩ ክፍተቶች ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግብረ-መልስ የሰጠበትን ማስረጃ ለማግኘት አልተቻለም፡፡

**<u>ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአሠራር መመሪያ አውጥቶ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ማሳወቁንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋገጠ መሆኑን በተመለከተ፣</u>**

23. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

24. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃዎች ፍተሻ የአሰራር መመሪያ ታህሳስ 8 / 2005 በደብዳቤ ቁጥር 011.34/1089 ስለማውጣቱ የሚያሳይ ማስረጃ ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ያቀረበ ቢሆንም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር ከሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ጉዳዩን አስመልክተው በሰጡት መልስ የአዳማ ቅ/ጽ/ቤትና የሞጆ ተወካይ ጽ/ቤት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ዝርዝር የሆነ የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቶ ያልተላከላቸው በመሆኑ ስራን ለይቶ ለማከናወን ችግር የፈጠረባቸው መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

25. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያወጣውን የደረጃዎች ፍተሻ መመሪያ በማሻሻል ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የሚያስችል ግልጽ በሆነና በማያሻማ መልኩ አዘጋጅቶ በሥሩ ለሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ሊያሰራጭና በትክክል ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

26. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር የአፈፃፀም መመሪያውን ለሁሉም ቅ/ፅ/ቤቶች ከሀምሌ 2008 ዓ.ም ጀምሮ ለማሰራጨት መወሰኑን ገልጿል፡፡

27. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

28. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የአሠራር መመሪያ የሌለ መሆኑን፣ የአሰራር መመሪያው በረቂቅ ደረጃ የሚገኝ እንደሆነ በንግድ ሚኒስቴር የሞጆ ቅ/ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች መግለፃቸውን፣ የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የስራ ኃላፊ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የአሠራር መመሪያ የሌለው መሆኑን፣ ስራው እየተሰራ ያለው በደረጃው መሰረት እንደሆነና መመሪያው ያልፀደቀና በረቂቅ ደረጃ መሆኑን፣ የአሰራር መመሪያ ባለመኖሩም የቅጣት ደረጃዎችን ለመወሰን አለመቻሉን፣ የንግድ ሚኒስቴር የሚወስደው እርምጃ እና የሥራ ሃላፊነት እንዳይታወቅ ማድረጉን፣ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የአሠራር መመሪያ የሌለው መሆኑን፣ አሁን እየተሰራ ያለውም በደረጃው እንደሆነ እና መመሪያ ባለመኖሩም በወጪና ገቢ እቃዎች የደረጃ ስራ ፍተሻ በየቅርንጫፉ ወጥ በሆነ መንገድ እንዳይሰራ ማድረጉን የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

29. አንዳንድ አስገዳጅ ደረጃዎች ለአተረጓገም አሻሚ መሆን የቁጥጥር ስራውን ወጥነት ያለው እንዳይሆን ማድረጉን፣ መጠናቸው አነስተኛ የሆኑ እና ለግልና ለኢንቨስትመንት ከውጭ ሀገር የሚመጡትን አስገዳጅ ደረጃ የወጣላቸው ምርቶችን ለመወሰን ወጥ የሆነ መመሪያ አለመኖሩን፣ የቁጥጥር ስራው ወጥ ያልሆነና ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ የተለያየ መሆኑን፣ የተለያየ የሪፖርት ፎርማት መከተል

መኖሩን፣ የአሰራር ማንዋል አለመፅደቁን፣ የአስገዳጅ ደረጃ የማስፈፀሚያ እና የህጋዊ ስነ ልክ አዋጅ እስካሁን አለመፅደቁ ከንግድ ሚኒስቴር ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. እንዲሁም ህጋዊ ስነ-ልክን በተመለከተ ደንብና መመሪያ ባለመኖሩ በሚዛንና በነዳጅ ዙሪያ ችግር መፈጠሩን፣ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ምርቶቹን ለመቆጣጠር የሚያስችል አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ማስፈጸሚያ ረቂቅ አዋጅ እና የቴክኒክ ደንብ በተቀመጠለት ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ አለመፅደቁ ታውቋል፡፡

31. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አስገዳጅ ደረጃ ያላቸዉ ምርቶች ወደ ሀገር ዉስጥ ሲገበና ሲወጣ የጥራት ቁጥጥር የሚደረገዉ የአስገዳጅ ደረጃዉን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በዋነኛነትስራው የአስገዳጅ ደረጃዉን መሰረት አድርጎ የሚሰራ መሆኑን፣ በአስገዳጅ ደረጃዉ ላይ የሚታዩትን ክፍተቶችና ተጨማሪ የአሰራር ስርዓቶች በቅ/ጽ/ቤቶች አንድ አይነት አተገባበር እንዲኖር በ2005 ዓ.ም የተዘጋጀ መመሪያ ያለ መሆኑን ፣ ከዚህም በተጨማሪ አዲስ የተሻሻለ የአሰራር መመሪያ በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ የአስገዳጅ ደረጃ አዋጁ ሲጸድቅ የአሰራር መመሪያዉም በቀጣይነት የሚጸደቅ እንደሚሆን ገልፀዋል ፡፡

32. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የክትትል ኦዲት ቡድኑ በናሙና ባያቸው የሞጆ፣ የአዳማ እና የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤቶች የአሰራር መመሪያው አለመኖሩን እና እየተሰራበት አለመሆኑን የገለፁ ቢሆንም በዋናው መ/ቤት ግን ታህሳስ 06 2005 ዓ.ም የፀደቀ መመሪያው መኖሩ እና ለክልሎች የተላከ ስለመሆኑ የሚያሳይ ደብዳቤ ለማየት ተችሏል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በሰው ኃይል እንዲደራጁ በማድረግና ለሥራው የሚሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረጉን <u>በተመለከተ፣</u>**

33. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

34. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በእስትራቴጂክ ዕቅዱና ዓመታዊ ዕቅዱ ላይ የሰው ሃብት በቁጥር፣ በዕውቀት፣ በክህሎት እና አመለካከት በማጐልበት የማስፈፀም አቅምን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ቢያቅድም በዕቅዱ መሠረት በሥሩ ያሉትን ቅ/ጽ/ቤቶች በሰው ኃይል በማደራጀት፣ ለሥራው የሚሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት እና በቂ በሆነ

ሥልጠና ክህሎታቸውን በማሳደግ አፈጻጸማቸውን እየተከታተለ አለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

35. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሥሩ ያሉትን ቅ/ጽ/ቤቶችን የማስፈጸም አቅምን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስና ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወን በተሟላ የሰው ኃይል በማደራጀትና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

36. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በዋናው መ/ቤትና በቅ/ፅ/ቤቶች ላይ የሚታየውን የሰው ሀይልና የግብዓቶች ክፍተቶች በቅጥር ለማሟላት በ2009 በጀት ዓመት በእቅድ መያዙን ገልጿል፡፡

37. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

38. በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት የሰው ኃይል የተሟላ መሆኑን እና ለሥራው የሚሆኑ መገልገያዎች/ግብዓቶች/ እንዲሟሉ የተደረገ ሲሆን ያለው ላብራቶሪ አንድ ብቻ በመሆኑ የውጤት መዘግየት የሚፈጠር በመሆኑ በዚህም የተነሳ ደንበኞች ቅሬታ እያቀረቡ እንደሚገኙ፣ በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የሰው ሀይል ችግር የተቀረፈ መሆኑን፣ ነገር ግን የኮምፒውተር እጥረት፣ የኢንተርኔት አለመኖር፣ የጠረጴዛና የወንበር እጥረቶች መኖራቸውን፣ በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የግብዓት፣ የክህሎት/የዕውቀት/ ክፍተቶች፣ የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ በወቅቱ አለመድረስ፣ የተሽከርካሪ ችግር፣ ክፍተቶች መኖራቸውን ለሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ታውቋል፡፡

39. በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የሰው ኃይል እና ለስራ የሚሆኑ መገልገያዎችን አለሟሟላቱን፣ በቅ/ፅ/ቤቱ በሰው ሀይል በኩል ፀሀፊ፣ የሒሳብ ሰራተኛ፣ ካሸር፣ ጥበቃ የሌለ መሆኑን፣ ተሽከርካሪ ባለመኖሩም ናሙና ለመውሰድ ከሀዋሳ ሻሸመኔ ድረስ በትራንስፖርት እየሄዱ የሚሰሩ እንደሆነ፣ በቂ የሠው ሀይልና የሥራ መገልገያዎች ባለመኖራቸው ስራቸውን በቅልጥፍና እንዳይሰሩ ማድረጉን፣ በበከልቻ ተወካይ ፅ/ቤት የገንዘብ ያዥ፣ ፀሀፊ፣ የሂሳብ ባለሞያ፣ የፅዳት ባለሞያ ተሟልቶ አለመቀጠሩን፣ ለአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የፅዳት እና የጥበቃ ሰራተኛ አለመቀጠሩ ታውቋል፡፡

40. የአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች የአዳማ ንግድ ሚ/ር ቅ/ፅ/ቤት በሰው ሀይል የተደራጀ አለመሆኑን እና ሳይት ላይ በመሄድ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑን ሲሆን በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በሚፈለገው ደረጃ ተሟልቶ አለመገኘቱን፣ የገንዘብ ተቀባይ ባለመኖሩ ስራው ለረጅም ጊዜ በተደራቢነት በሌላ ሰራተኛ እየተሰራ መሆኑን፣ በተጨማሪም ፀሀፊና የሂሳብ ሰራተኛ አለመኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

41. እንዲሁም የተሽከርካሪ ችግር በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በዋናው መ/ቤት አሁንም መሰረታዊ መፍትሄ ያላገኘ ችግር መሆኑን፣ በዋናው መ/ቤት፣ በቅ/ፅ/ቤቶችና በህጋዊ ስነ ልክ ቡድን በየሥራ ዘርፉ የሰው ሀይል እጥረት በመኖሩ ቅጥር እንዲፈፀም በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም እስካሁን አለመፈፀሙን፣ በአንዳንድ ቅ/ፅ/ቤቶች የቢሮ ጥበት መኖር እና ለስራ አመቺ ያልሆነ የሥራ ቦታ መኖሩንየደንበኞች ናሙናዎች ከተወሰደ በኋላ ላቦራቶሪ በወቅቱ አለመድረስና ነጋዴውን ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉን ከንግድ ሚኒስቴር ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

42. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ ያለውን የሰው ሀይል አለሚሟላት ችግር ለመቅረፍ በድርጊት መርሃ-ግብሩ በታቀደው መሰረት በተከታታይ በተወሰዱ የማሻሻያ ስራዎች ቁጥራቸው ከ 20 በላይ የሆኑ የአዳዲስ ሰራተኞችን ቅጥር በማካሄድ በተጨማሪ ከ10 በላይ ሰራተኞችን በዝውውር በመመደብ ችግሩን ለመቅረፍ መሰራቱን እና አሁን እየተሰራ እንደሚገኝ፣ በዘርፉ ከሚታየው የሠራተኛ ፍልሰት አንፃር ችግሩን ሰፊ ማድረጉ፣

43. ለዚህም ችግር እንደምክንያት የሚጠቀሰው በዘርፉ ያለው አነስተኛ የደሞዝ አከፋፈል ስርዓት መኖሩ የሠራተኛውን ፍልሰት ከፍተኛ ማድረጉን፣ ይሁንና ችግሩን ለመፍታት አሁንም እየተሰራ እንደሚገኝ፣

44. በቅርንጫፍ ፅ/ቤት የሚታየውን የግብዓት ክፍተቶች ለመቅረፍ በተለያየ ጊዜ በተወሰዱ እርምጃዎች ችግሩን ለመፍታት ጥረቶች መደረጋቸውን፣ የተለያዩ የቢሮ መገልገያ ቋሚ ዕቃዎች ኮምፒውተር፣ መንበር፣ ጠረጴዛና የመሳሰሉ እቃዎችን ከሌሎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ካሉ የሥራ ዘርፎች ቅድሚያ በመስጠት ለቅ/ፅ/ቤቶቹ የማከፋፈል ስራዎች በተከታታይ መሰራታቸውን፣ ይሁንና ዘርፉ ሰፊና ውስብስብ እንደመሆኑ ከአቅም ውስንነት አንፃር አሁንም ያልተፈቱ ችግሮች ቢኖሩም በሂደት

እየተፈቱ የሚስተካከል መሆኑን፣ በተለይም የተሽከርካሪ ችግር አሁንም እንደችግር የቀጠለ ቢሆንም ከስራ አንገብጋቢነት አንፃር ለተወሰኑ ቅርንጫፎች ቅድሚያ በመስጠት ከሌሎች የስራ ክፍሎች በትውስት በመውሰድ ችግሩን ለማቃለል እየተሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

45. ይሁን እንጂ በናሙና በታዩ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የሰው ሀይል እጥረት እና የግብዓት ችግር ያልተቀረፈ መሆኑን የክትትል ኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡

***ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ የገቢ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊትና ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ገበያ ላይ ከመዋላቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጡን በተመለከተ፣***

46. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

47. የወጪ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲሁም የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት እንዲወጡ አልፎ አልፎ የማይደረግበት ሁኔታ መኖሩን፣

48. በሚ/ር መ/ቤቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ጥራታቸውን ለማረጋገጥ የሚበጠሩበት አንዳንድ የማበጠሪያ ቤት መጋዘኖች ናሙና ለመውሰድ በሚያመች መልኩ ያልተደረደሩ መሆኑ፣ እንዲሁም ማበጠሪያ ቤቶች ወቅቱን ጠብቀው የንግድ ፈቃድ እድሳት አለመፈፀማቸው የተቀላጠፈ አገልግሎት ባለመሥጠትና በምርት ጥራት ላይ ተጽዕኖ የፈጠረ በመሆኑ፣ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ስለመቆጣጠሩና ስለመከታተሉ የሚያረጋግጥ የክትትል ሥራ አለመሰራቱ ተገኝቶ ነበር፡፡

49. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ምርቶች ከሃገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸውና ጥራታቸውን የጠበቁ መሆኑን የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የማበጠሪያ ቤቶችን የሥራ እንቅስቃሴና በየጊዜው ፈቃድ ማሳደሳቸውን የሚከታተል መሆኑን የሚቆጣጠርበት ስርዓት ሊኖረውና እንዲሁም ገቢ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት የሕብረተሰቡን ጤንነትና የአካባቢ ደህንነት ከማስጠበቅ አንጻር በጉምሩክ ጣቢያዎች ደህንነታቸውና ጥራታቸው የጠበቁና ተገቢውን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ ምርቶች የሀገሪቱን

ህግና ደንብ ተከትለው መግባታቸውን (መለካታቸውን) በማረጋገጥ ይሁንታ (Permit) ሊሰጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

50. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው ምርቶች ጥራታቸው በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ሳይረጋገጥ ወይም የሦስተኛ ወገን የጥራት ሰርተፊኬት ሳይቀርብ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበትም ሆነ ከሀገር የሚወጡበት አሰራር ከሚያዚያ 2008 ዓ.ም ጀምሮ የቆመ መሆኑን ገልጿል፡፡

51. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

52. በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት የወጪ ምርቶች የሌሉ ሲሆን በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የወጪ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው እንዲሁም የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት የሚወጡ መሆናቸውን፣ ቅ/ፅ/ቤቱ ናሙና ከወሰዱ በኋላ ለተስማሚነት ምዘና ድርጅት በኮድ እንደሚሰጡ እና በሚሰጠው ውጤት መሰረት ወደ ውጪ እንዲወጣ እንደሚደረግ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ቢገልፁም ማስረጃውን ለኦዲት ቡድኑ አለመቅረቡን ፣

53. እንዲሁም ከእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት ወደ ውጪ የሚላኩና በእይታ ብቻ የሚስተናገዱ እንደ አትክልትና ፍራፍሬ የምርት ጥራታቸው ያልተጠበቀ እንደሆነ እና እርምጃ ወስዶ ለማስተካከል አስቸጋሪ (በቀላሉ ወደ ህገ-ወጥ ንግድ መጋለጥ መቻሉን) ታውቋል፡፡

54. የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች የወጪ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው እንዲሁም የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት የሚወጡ መሆናቸውን፣ ቅ/ፅ/ቤቱ ከመጋዘኖች ናሙና በመውሰድ ለተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሚልክ እንደሆነ እና ምርቱ ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት የላብራቶሪ ውጤት ሲመጣላቸው ብቻ ምርቶች እንዲወጡ እንደሚደረግ በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ጥያቄ የገለፁ ቢሆንም ማስረጃውን አላቀረቡም፡፡

55. የማበጠሪያ ቤቶችን በተመለከተ በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በ2009 ዓ.ም 13 ( አስራ ሶስት) ፈቃዳቸውን ያላደሱ ማበጠሪያ ቤቶች መኖራቸውን የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት በ2010 ዓ.ም ደግሞ 34 የሚሆኑ የንግድ ማበጠሪያ ቤቶች መኖራቸውን ከእነዚህም መካከል የንግድ ፈቃዳቸውን ያላሳደሱ 14 ማበጠሪያ ቤቶች መኖራቸውንና ይህንንም ለአዳማ ንግድ ሚ/ር ቅ/ፅ/ቤት ያሳወቁ መሆናቸውን እና ናሙና የሚወሰደው በንግድ ሚ/ር መሆኑን የአዳማ የተስሚነት ምዘና ድርጅት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች እና ከማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡፡

56. እንዲሁም በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ፍቃዳቸውን ያላሳደሱ 6 ማበጠሪያ ቤቶች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ያገደ መሆኑን ፣ <u>ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ፣</u>**

57. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

58. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢ ዕቃዎችን በተመለከተ የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የላብራቶሪ ውጤት ወይም በዓለም አቀፍ ሶስተኛ ወገን ሠርተፊኬት አምጥተው ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ደረጃቸውን የማያሟሉ መሆናቸው ተረጋግጦ እንዲታገዱ ከተደረገ በኋላ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጁ ከተደነገገው በተቃራኒ ደብዳቤ በመጻፍ እንዲለቀቁ የሚያደርግ መሆኑን፣ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ውጤቱን ሲልክ ዕቃዎቹ የኢትዮጵያ ደረጃ የማያሟሉና ቀድመው የሚለቀቁ በመሆኑ በህጉ መሠረት ጥራታቸው ሳይረጋገጥ ወደ ገበያ ገብተው ለተጠቃሚው የሚደርሱ መሆናቸውን ተገኝቶ ነበር፡፡

59. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው ምርቶች አስፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ ገቢ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ በተስማሚነት ምዘና ድርጅት ተፈትሸው ማለፋቸውን በማረጋገጥ ደረጃ የማያሟሉ ምርቶች እንዳይገቡ ሊያደርግና ፣ እንዲሁም ከደረጃ በታች በሆኑት ላይ በህብረተሰቡ ጤናና የአካባቢ ደህንነትን ከማስጠበቅ አንጻር በመቆጣጠር ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

60. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በጊዜያዊ መልቀቂያ ምርቶች የሚለቀቁበት አሰራር ከመጋቢት 2008 ዓ.ም ጀምሮ የቆመ መሆኑን እንዲሁም ከመጋቢት 2008 ዓ.ም ጀምሮ ከደረጃ በታች ሆነው በተገኙ ምርቶች ላይም ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በመቀናጀት እንዲታገዱ እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡

61. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

62. በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ገቢ ምርቶች አለመኖራቸውን ፣ በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት አሁን ላይ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ተገቢውን መስፈርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር ውስጥ እንደማይገቡ፣ በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት ከውጪ የሚገቡ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደህንነታቸውና ጥራታቸው እንዲሁም ተገቢውን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን ተረጋግጦ መሆኑን እና ከዚህ ቀደም የነበረው የኮሚትመንት አሰራር የቀረ መሆኑን የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች የገለፁ ቢሆንም ማስረጃውን ለኦዲት ቡድኑ አላቀረቡም፡፡

63. የሞጆ እና የአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ከውጪ የሚገቡ ምርቶች ደረጃቸው ሳይረጋገጥ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ እንደማይደረግ፣ ባለጉዳዮች ከንግድ ሚ/ር የጥራት ማረጋገጫ እንዲያመጡ ከተደረገ በኋላ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የሚደረግ መሆኑን ቢገልፁም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

64. ደረጃቸውን ያላሟሉ የገቢ ንግድ እቃዎች ለጉምሩክ ደብዳቤ በመፃፍ እንዲታገዱ እንደሚደረግ እና በጥራት ችግር ምክንያት አይለቀቁም ተብለው የታገዱ ምርቶች በንግድ ሚ/ር ዋናው መ/ቤት በኩል እንዲለቀቁ ደብዳቤ የሚፃፍበት ሁኔታ መኖሩን፣

65. በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የወጪና የገቢ ንግድ  ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ  የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ  እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ /እንዲታገዱ/ ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ደብዳቤ የሚያሳውቁ መሆኑን ፣ነገር ግን ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በደብዳቤ ከማሳወቅ ውጪ የታገደው እቃ ስላለበት ሁኔታ የማያውቁ እንደሆነ፣

66. በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የገቢ ምርቶች የሌሉ ሲሆን የወጪ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት ያላሟሉ ምርቶቹ ከሀገር እንዳይወጡ እንደሚታገዱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

67. ንግድ ሚኒስቴር በህጋዊ ስነ-ልክ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ካላቸው የመለኪያ መሳሪያዎች ውስጥ አንደኛው የውሃ ቆጣሪ / Water meter / ሲሆን በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን በላብራቶሪ ተፈትሾ በውጤታቸው መሠረት እንዲስተናገዱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚያዚያ 10 ቀን 2008 ዓ.ም ለቅ/ፅ/ቤቶችና ለወኪል ፅ/ቤቶች ደብዳቤ መፃፉ፣ ይሁን እንጂ የውሃ ቆጣሪ / Water meter / የደረጃ መስፈርት ላይ አወሳሰን ክፍተት የፈጠረ በመሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ ለኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ደረጃው እንዲዘጋጅ ጥያቄ ማቅረቡን እና ደረጃው በዝግጅት ሒደት ላይ ስለሚገኝ ደረጃውም ተዘጋጅቶ እስከሚወጣ ድረስ ለጊዜው በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን መ/ቤት የላብራቶሪ ፍተሻ ማስደረጉ ቀርቶ በእይታ ፍተሻ / Visual Inspection / ብቻ ባለጉዳዮች እንዲስተናገዱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መጋቢት 11 ቀን 2009 ዓ.ም ለሁሉም ቅ/ፅ/ቤቶች ደብዳቤ የፃፈ መሆኑ ታውቋል፡፡

68. እንዲሁም የፀሀይ ኢንዱስትሪ ኢ.ማ. የቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ በኢንቮይስ ቁጥር J-1608-008 DTD እ.ኤ.አ ነሀሴ 08/2016 እና በዲክላራሲዮን ቁጥር C-25329 እና C- 26798 የተመዘገበ ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቡት ለኮርኒስ ፍሬሞች፣ ለመፃህፍት መደርደሪያዎችና ለኬብል ትሬይ የሚገለገሉበት የተጠቀለለ ልሙጥ የዚንክ ቅብ ቆርቆሮ (coil) በ CES 40 አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ መሰረት በላብራቶሪ ተፈትሾ የደረጃውን መስፈርት አላሟላም በማለት ጥሬ እቃው እንዳልተለቀቀላቸው በመግለፅ በመቸገራቸውና ቀጣይ የማምረት ሂደት ማከናወን ባለመቻላቸው መፍትሔ እንዲሰጣቸው አቤቱታ ማቅረባቸውን፣

69. የንግድ ሚኒስቴር የማኔጅመንት ኮሚቴው ፀሀይ ኢንዱስትሪ ኢ.ማ የቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ በፋብሪካው ግቢ የተራገፈው የተጠቀለለ ልሙጥ የዚንክ ቅብ ቆርቆሮ በምን ስራ ላይ እንደዋለ ከሪጉላቶሪ ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ጽ/ቤት እና ከገበያና ድርጅት ኢንስፔክሽን ባለሞያዎች ከአመራሩ በተሰጠው አቅጣጫ በማምረቻ ቦታው ተገኝተው ከላይ የተጠቀሰው ቆርቆሮ በምን አግባብ ጥቅም ላይ እየዋለ እንዳለ ሪፖርት መቅረቡን፣

70. ኮሚቴው በባለሞያዎች የቀረበውን ሪፖርት በመገምገምና አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ CES40 በአንቀፅ 6.2 የተቀመጠው መስፈርት በግርጌ ማስታወሻ እንደተገለፀው የደረጃው ተፈፃሚነት ለቤት ክዳን ቆርቆሮ ብቻ መሆኑን ከግንዛቤ በመውሰድ ፋብሪካው ያስመጣው የተጠቀለለ ልሙጥ የዚንክ ቅብ ቆርቆሮ ከመደበኛው የጣሪያ ቆርቆሮ ማምረት ውጪ ለኮርኒስ ፍሬሞች፣ ለመፃህፍት መደርደሪያዎችና ለኬብል ትሬይ ምርቶች በግባዓትነት ሊጠቅም እንደሚችል ኮሚቴው የፈቀደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

71. ኮምቦልቻ ብረታ ብረት ምርቶች ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ ቀደም ሲል በነበረው አሰራር ለጣሪያ ክዳን የማይውል ቆርቆሮ የጥራት ደረጃ ፍተሻ የመይከናወን በመሆኑ ጥሬ እቃው መንግስት አምራች ድርጅቶችን ለማበረታታት የውጭ ፍተሻ በፈቀደው መሰረት በፋብሪካው ግቢ በመራገፉ የማምረት ሂደት ወዲያውኑ በመከናወኑ ለጥራት ቁጥጥር ፋብሪካው ናሙና ሲጠየቅ ምርቱን ለገበያ በማዋሉ የላብራቶሪ ፍተሻ ተከናውኖ ጥራቱን ማረጋገጥ ባለመቻሉ ሙሉ መልቀቂያ አለመሰጠቱን እና አዲሱን አሰራር በመገንዘብ የተፈፀመ ስህተት መሆኑን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመገንዘብ መልቀቂያ እንዲሰጠው ፋብሪካው ማመልከቱን፣

72. በገቢና ወጪ እቃዎች ጥራት ቁጥጥር በኩል የምርት ጥራት ቁጥጥር ሳይደረግ ፋብሪካው ጥሬ ዕቃውን ጥቅም ላይ ማዋሉን ፣ በመሆኑም ከገቢና ወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር እና ከገበያና ድርጅት ኢንስፔክሽን ሪጉላቶሪ ዳይሬክቶሬት የተውጣጣ የባለሞያ ቡድን በፋብሪካው ቅጥር ግቢ በመገኘት ምልከታ ያደረገ ሲሆን ቡድኑ ያቀረበውን ሪፖርት የማኔጅመንት ኮሚቴው በዝርዝር መመልከቱን፣

73. በሪፖርቱም ከባለሞያዎች እንደተመለከተው ፋብሪካው በዲ/ዮን ቁጥር C-47713 ወደ ሀግር ውስጥ ያስገባው ባለ 0.5 ሚ.ሜ 46 ጥቅል (colil) የዚንክ ቅብ ልሙጥ ቆርቆሮ የላብራቶሪ ፍተሻ ሳይከናወንበት ለምርት አገልግሎት በማዋል ለገበያ ያሰራጨው በመሆኑ ምንም ዓይነት ናሙና በቡድኑ ሊወሰድ እንዳልቻለ ግንዛቤ መወሰዱ ፣

74. በመሆኑም የነበረውን ግድፈት የማኔጅመንት ኮሚቴው ፋብሪካው እስከዛሬ ያስመዘገበው የጥራት ሪከርድ በመገምገም በጥሩ ደረጃ የሚገኝ መሆኑ መረጃውን በመመልከትና ምርቱ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ በሦስተኛ ወገን SGS ተፈትሾ የጥራት ደረጃውን ያሟላ መሆኑን በሠርተፊኬት በመረዳት የማኔጅመንት ኮሚቴው ፋብሪካው

ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደግም ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው በማስገንዘብ መፍቀዱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

75. ኖርክ አግሮ ኢንዱስትሪያል ኃ/የ/የግል ማህበር ከውጭ ሀገር ያስመጣው አምስት ጥቅል ቆርቆሮ (5 coli) በቤት ክዳን ቆርቆሮ ደረጃ በ CGS40፡2015 ተፈትሾ የኢትዮጵያ ደረጃ አላሟላም ተብሎ መውደቁን ፣

76. ይሁንና ድርጅቱ ምርቱን የሚጠቀመው የቤት ክዳን ቆርቆሮ ለማምረት ሳይሆን በፋብሪካ ለሚከናወነው የምግብ ማሸጊያ ( Food Canning ) በመሆኑ እና አስመጪው የቆርቆሮ አምራች ባለመሆኑ እነዲሁም የምርቱ ብዛት አነስተኛ በመሆኑ ያስመጡት ምርት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ የቀረበ ሲሆን የንግድ ሚኒስቴር የማኔጅመንት ኮሚቴው ምርቶቹ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የመጡ እቃዎች በመሆናቸው እና መጠናቸውም አነስተኛ በመሆኑ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ውሳኔ መስጠቱ ታውቋል፡፡

77. ጂኢሲ ስቲል ኤም.ኤስ ጂ ኃ/የተ/የግል ማህበር ለኢንቨስትመንት ካስመጣው የአርማታ ብረት ውስጥ ባለ ስምንት ሚ.ሜ ዲያሜትር በmass per lenegth ፓራሜትር የኢትዮጵያ ደረጃ ያለማሟላቱን፣

78. ይሁንና የድርጅቱ ዋናው ግንባታ የተጠናቀቀ በመሆኑ ለሌሎች ቀሪ ስራዎች ለማሽነሪ ማስቀመጫ አገልግሎት ለሚያውለው ቀላል ግንባታ የሚጠቀምበት በመሆኑ፣ አርማታ ብረቱ ለራሱ ኢንቨስትመንት አገልግሎት ብቻ የሚውል እና የምርቱም ብዛት አነስተኛ (ከ25 ሜትሪክ ቶን) በመሆኑ ያስመጡት ምርት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ መቅረቡን፣ የንግድ ሚኒስቴር የማኔጅመንት ኮሚቴው ምርቶቹ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የመጡ እቃዎች በመሆናቸው እና መጠናቸውም አነስተኛ በመሆኑ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ውሳኔ መስጠቱ ታውቋል፡፡

79. ኢ.ቲ.ኢ.ኤስ ኢንዱስትሪያል ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግል ማህበር ከውጭ ሀገር ያስመጣቸው ጥቅል ቆርቆሮ በኢትዮጵያ ደረጃ CGS40፡2015 በላብራቶሪ ተፈትሾ ዝቅተኛውን የዚንክ ቅብ መጠን ባለሟሟላቱ ወደ ሀገር እንዳይገባ መታገዱን፣

80. ይሁንና ምርቱ ለቤት ክዳን ቆርቆሮ ማምረቻነት ሳይሆን ለተገጣጣሚ የመጋዘን ፓርቲሽንና ለኮርኒስ አገልግሎት በመሆኑ እና ያመጣቸውም ብዛት 23 ኮይል ብቻ በመሆኑ ያስመጡት ምርት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ መቅረቡን ፣ የንግድ ሚኒስቴር የማኔጅመንት ኮሚቴው ምርቶቹ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የመጡ እቃዎች በመሆናቸው እና መጠናቸውም አነስተኛ በመሆኑ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ውሳኔ መስጠቱ ታውቋል፡፡

81. ከደረጃ በታች በተገኙ ምርቶች የሚወሰድ እርምጃን በተመለከተ የሞጆ ቅ/ፅ/ቤት ከደረጃ በታች የሆኑ ምርቶች ሲኖሩ ለጉምሩክ እና ለሚ/ር መ/ቤቱ በደብዳቤ እንደሚያሳውቁ እና ከደረጃ በታች የሆነው ምርት እንደሚወገድ ፣ የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ እንደማይወሰድ እና እርምጃ የሚወስደው የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

82. አንዳንድ አስገዳጅ ደረጃዎች መስፈርት ግልፅ አለመሆኑ ለውሳኔ አሰጣጥ አስቸጋሪ ስለሆነ ለማጣራት በሚደረገው ሂደት ተገልጋዩ ተጨማሪ የመጋዘን ለመክፈል መገደዱን ከአዳማ ቅ/ፅ/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት ታውቋል፤፤

83. የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን የሚቆጣጠር መሆኑን እና ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው የተገኙት ላይ የሚወሰድ እርምጃ የይለፍ ወረቀት ከመከልከል ውጪ ሌላ የሚወስዱት እርምጃ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

**የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳወቁንና ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን፣ ናሙናዎች ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት <u>ላብራቶሪ እንዲቀርቡ ማድረጉን በተመለከተ፣</u>**

84. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

85. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳወቁን ሊከታተልና ሊቆጣጠር የሚገባ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ይህንን ጉዳይ ተግባራዊ አለማድረጉ ተገኝቶ ነበር፡፡

86. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ድርጅት ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት እንደ የዕቃዎቹ አይነትና ባህሪ በተቀመጠላቸው ጊዜ ውስጥ በመፈተሽ ውጤታቸውን መግለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳውቁን ሊከታተልና ሊቆጣጠርና እንዲሁም አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በሚያዘው መሰረት የተወሰዱ ናሙናዎች ከውጫዊ ተፅኖ ነጻ ሆነው የጥራት ባህሪያቸው ሳይለወጥ ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ለፍተሻ እንዲቀርቡ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

87. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ላይ ቁጥጥር የማድረግ ስልጣንና ሃላፊነት የሌለው መሆኑን ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከድርጅቱ ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከር የላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ እንዲያሳውቅ በየጊዜው በመገናኘት ያሉትን ክፍተቶች ለመቅረፍ ውይይት እየተካሄደ እንደሚገኝ፣

88. እንዲሁም ከተስማሚነት ምዘና ድርጅቱ ጋር በየሩብ ዓመቱ የውይይት መድረክ ለማዘጋጀት በ2009 በጀት ዓመት በዕቅድ መያዙን፣ በቅ/ፅ/ቤቶች ናሙና ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ውስጥ ለላብራቶሪ ምርመራ ቶሎ እንዲቀርቡ ያለውን የተሽከርካሪ እጥረት በማሟላት ችግሩን ለመቅረፍ በ 2009 በጀት ዓመት በዕቅድ መያዙን ገልጿል፡፡

89. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

90. ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለመረዳት እንደተቻለው በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት ተደራራቢ የፍተሻ ጥያቄዎች ሲኖሩ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የፍተሻ ውጤት መግለፅ ባለበት ጊዜ የማያሳውቅ መሆኑን፣ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት የሚያዘገይ መሆኑን፣ በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ያለው ላብራቶሪ አዲስ አበባ ብቻ አንድ በመሆኑ የላብራቶሪ ውጤት እንደሚዘገይ፣ በዚህም ምክንያት ደንበኞች ለተጨማሪ የዲሜሬጅ ወጪ መዳረጋቸውን ፣

91. በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳወቁን መከታተልና መቆጣጠር ላይ ክፍተት መኖሩን እና የላብራቶሪ ውጤት የሚዘገይ እደሆነ ታውቋል፡፡

92. የላብራቶሪ ፍተሻ የሚደረገው አዲስ አበባ ብቻ በመሆኑ ፣ በንግድ ሚ/ር አዳማ ቅ/ፅ/ቤት የሎጀስቲክ እጥረት በመኖሩ ፣ የላብራቶሪ ውጤት የሚፈልጉ እቃዎች ውጤታቸው ረጅም ጊዜ (እስከ አንድ ወር ድረስ) እንደሚዘገዩ ፣ የተወሰዱ ናሙናዎች ለባለቤቶቹ እንደማይመለሱ እና አንዳንድ ናሙናዎች ከመጠን በላይ የሚወሰዱ እንደሚወሰዱ፣ በዚህም ምክንያት ተገልጋዮችን ለመጋዘን ኪራይ ወጪ በመዳረጉ ተገልጋዮች መማረራቸውን በተጨማሪም ቀልጣፋ የጉምሩክ አገልግሎት እንዳይሰጥ መከልከሉን የአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

93. የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የመፈተሻ አቅም ውስንነት ምክንያት አሁንም የላብራቶሪ ውጤቶች እንደሚዘገዩ፣ በፀሀይ ሀይል የሚሰሩ የሶላር መገልገያዎች የጥራት ደረጃቸው እንዲረጋገጥ ለኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ላብራቶሪ ናሙና ተሰጥቶ ውጤት ሳይገለፅ ከሁለት አመት በላይ በመሆኑና ተገላጋዮች ለዋስትና ያስያዙት ገንዘብ ባለመመለሱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይ ደንበኞች በተደጋጋሚ ቅሬታ ማንሳታቸውን ፣

94. እንዲሁም የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የላብራቶሪ የፍተሻ አቅም ውስንነት ምክንያት ከ 24 ሚ.ሜ በላይ የሆኑ የአርማታ ብረቶች በሀገር ውስጥ የመፈተሻ አቅም አለመኖሩን እና ከየፋብሪካዎች የሚወስደው ናሙና ፈትሾ ለፋብሪካዎችም በወቅቱ እንደማይልክ ለማወቅ ተችሏል፡፡

95. የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች የተወሰዱ ናሙናዎች ከውጫዊ ተፅኖ ነጻ ሆነው የጥራት ባህሪያቸው ሳይለወጥ ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ለፍተሻ ላብራቶሪ መቅረባቸውን በተመለከተ በሞጆ እና በሀዋሳ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የተወሰዱ ናሙናዎች በተወሰዱ በ48 ሰዓታት ውስጥ ለፍተሻ ላብራቶሪ እንዲቀርቡ የሚደረግ መሆኑን የገለፁ ሲሆን በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የተሽከርካሪ እጥረት ስላለበት ናሙናዎችን ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ወደ ፍተሻ ላብራቶሪ ለመውሰድ የማይችሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

96. በተጨማሪም የደንበኞች ናሙናዎች ከተወሰደ በኋላ ላቦራቶሪ በወቅቱ አለመድረስና ነጋዴውን ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉን ከንግድ ሚኒስቴር የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የላብራቶሪ ሰርተፊኬት እንዲያቀርቡ ማድረጉንና ፣ የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ያላቀረቡ አስመጪዎች የላብረቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ <u>በጉምሩክ እንዲጠብቁ ማድረጉን በተመለከተ፣</u>**

97. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

98. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህዳር 2/2006 ዓ.ም. ለቅ/ጽ/ቤቶች በፃፈው ደብዳቤ አሰገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ያላቸው ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ኢንስፔክሽ አካላት የተረጋገጠ የላብራቶሪ ሰርተፊኬት ከአገልግሎት መጠየቂያ ጋር እንዲቀርቡ በማድረግና የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ማቅረብ ግዴታ መሆኑ ከሁለት ጊዜ በላይ ተነግሯቸው ሰርተፊኬት ማቅረብ ያልቻሉ አስመጪዎች ምርታቸው የደረጃ መስፈርት ማሟላቱ የላብረቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ እንዲጠብቅ መደረግ ያለበት መሆኑን፣

99. ነገር ግን አንዳንድ ተገልጋዮች ከውጭ ለሚያስመጡት ዕቃ የሶስተኛ ወገን ሠርተፊኬት ሳያቀርቡ በነበረው አሰራር /በውዴታ ግዴታ/ እና የላብራቶሪ ውጤት ሳይገለጽ ምርቶች እየተለቀቁ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

100. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አሰገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ያላቸው ምርቶች አለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ኢንስፔክሽን አካላት የተረጋገጠ የላብራቶሪ ሰርተፊኬት ከአገልግሎት መጠየቂያ ጋር እንዲያቀርቡ በማድረግ ፣

101. የሰርተፊኬቱ ትክክለኛነት አንድ ሶስተኛ ወካይ ናሙና ወስዶ በላብራቶሪ ሊያረጋግጥና በሥሩ ለሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስመጪዎች ለሚያመጧቸው ዕቃዎች የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ማቅረብ ግዴታ መሆኑ ከሁለት ጊዜ በላይ ተነግሯቸው ሰርተፊኬት ማቅረብ ላልቻሉ አስመጪዎች ምርቶቹ ተለቀው በማህበረሰቡና በአከባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ በውዴታ ግዴታ እንዳይለቀቁ

የደረጃ መስፈር ማሟላታቸውን የላብራቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ ጣቢያዎች እንዲጠብቁ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

102. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር አስገዳጅ ደረጃ ኖሯቸው በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ላብራቶሪ ፍተሻ መደረግ የሚቻልባቸው ምርቶች የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ያቀረቡም ሆነ ያላቀረቡ ድርጅቶች ምርቶቹ በላብራቶሪ ተፈትሸው ጥራታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቀድ መሆኑን፣

103. ነገር ግን በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የላባራቶሪ ፍተሻ መደረግ የማይቻልባቸው አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ኖሯቸው የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ለቀረበላቸው ምርቶች ብቻ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ እየተደረገ እንደሆነ የሦስተኛ ወገን ላልቀረበላቸው ምርቶች ግን ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ከሚያዚያ 2008 ዓ.ም ጀምሮ በመደረግ ላይ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡

104. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

105. በሞጆ፣ በአዳማና በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የውዴታ ግዴታ አሰራር ከዚህ ቀደም የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ የውዴታ ግዴታ አሰራር የቀረ መሆኑን፣ እቃው የሚለቀቀውም የላብራቶሪ ውጤት ከመጣ በኋላ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

106. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መጋቢት 20/ 2008 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የገቢ ምርቶች በላብራቶሪ ባህሪያቸው በሚወስደው ረዥም ጊዜ፣ የላብራቶሪ ፍተሻ አቅም ውስንነት፣ በጉምሩክ አሰራር ላይ ጫና ላለመፍጠር፣ የጭነት መኪናዎች ጭነው ቆመው ተጨማሪ ወጪ እንዳይከሰት በሚል ታህሳስ 8 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መመሪያ በunder tracking በጊዜያዊ መልቀቂያ በተለምዶ የላብራቶሪ ፍተሻ በቅርበት በማይገኝባቸው ቅ/ፅ/ቤቶች ሲሰራ እንደነበር፣ ሆኖም አንዳንድ አስመጪዎች የላብራቶሪ ፍተሻ ተደርጎ ውጤቱ ሳይገለፅ ለገበያ እንደሚለቁ በመታወቁ በunder tracking ምርት በጊዜያዊነት እንዲለቀቅ የተላለፈው መመሪያ ተሰርዞ የምርቱ የጥራት ደረጃ ሲታወቅ ብቻ እንዲለቀቅ እና የግዴታ ውል ገብተው በጊዜያዊ መልቀቂያ ደንበኞችን ማስተናገድ የተከለከለ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

107. ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የላብራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት በማይሰጥባቸው ምርቶች እና አገልግሎቶች ላይ ይህ መመሪያ ተግባራዊ ስለማይሆን በሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ሲቀርብ ሙሉ መልቀቂያ በመስጠት ባለጉዳዮችን እንዲያስተናግዱ ንግድ ሚኒስቴር ሚያዚያ 7 ቀን 2008 ዓ.ም ለቅ/ፅ/ቤቶችና ለተወካይ ፅ/ቤቶች ከፃፈው ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

108. እንዲሁም የሞጆ ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በአሁኑ ሰዓት ያለው አሰራር እቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ በሞጆ ጉምሩክ ጣቢያ ተፈትሸው እንዲለቀቁ የሚደረግ መሆኑን እና በተስማሚነትና ምዘና ድርጅት ላብራቶሪ መፈተሽ የማይችሉ እንደ ሶላር መብራቶች፣ የውሃ ፓምፖች የመሳሰሉት እቃዎች ላይ የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት እንዲመጣ የሚደረግ ሲሆን የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ያላቀረቡ አስመጪዎች አለማቅረባቸውን ለጉምሩክ በደብዳቤ ብቻ እንደሚያሳውቁ እና ጉምሩክ እቃዎቹ እንዲወገዱ ወይም እንዲለቀቁ የሚያደርገው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

109. የሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች የሶስተኛ ወገን የሚጠየቀው በንግድ ሚ/ር ቅ/ፅ/ቤት መሆኑን እና ከዚህ ቀደም የነበረው ከፊል መልቀቂያ የቀረ እንደሆነ እና የላብራቶሪ ውጤት ውጤት እስከ አንድ ዓመት የሚዘገይበት ሁኔታም መኖሩን አስረድተዋል፡፡

110. ታማኝ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያላቸው የድርጅት እቃዎች ወደ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ስለማይመጡ የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ቁጥጥር እንደማይደረግ፣ ወደ ኩምሩክ መጋዘን የሚመጡት ግን የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ሳያቀርቡ እቃዎች እንደማይለቀቁ የአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የስነ ልክ ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ቁጥጥር ማድረጉን ፣ የመለኪያ መሣሪያዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና <u>በፌዴራል ተጠናክረው መሥራታቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ፣</u>**

111. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

112. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የስነ ልክ ስርዓት እንዲዘረጋና ተግባረዊ መደረጉን እንዲቆጣጠር በአዋጅ ስልጣን የተሰጠው ቢሆንም መ/ቤቱ የዘረጋው የሀገሪቱን የስነ

ልክ ስርዓት በክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ቢከናወንም ሸማቹ ኅብረተሰብ በተሻለ ሁኔታ ጥቅሙ እንዲጠበቅና አፈጻጸሙ ውጤታማ እንደሚሆን በማሰብ ለክልሎች ውክልና የሰጠ ቢሆንም ተግባራዊ መደረጉን ተገቢውን ቁጥጥር እያደረገ አለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

113. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን የሀገሪቱን የስነ ልክ ስርዓት ሊዘረጋና በሁሉም ውክልና በተሰጣቸው የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ተግባራዊ መደረጉን ቁጥጥር ሊያደርግና የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ሥራዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናክረው እንዲሠሩ በቂ የሆነ ስታንዳርድ የመለኪያ መሣሪያዎች ለክልሎችም ድጋፍ ሊያደርግ፣

114. እንዲሁም በክልሎችም የሕጋዊ ሥነ-ልክ ባለሙያዎች ያለባቸውን የክህሎት ክፍተታቸውን እንዲያሻሽሉ ትኩረት በመስጠት የስልጠ ድጋፍ ሊያደርግ እና የቬሪፊኬሽን ሥራ መሠራቱንም የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባየማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

115. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ክልሎች በእጃቸው የሚገኙትን ስታንዳርድ የመለኪያ መሳሪያዎች ካልብሬት የማስደረግ የራሳቸው ስልጣን መሆኑን፣

116. ክልሎች ያለባቸውን የባለሞያ ክህሎት ክፍተት ለመቅረፍ በ2009 በጀት ዓመት በሁሉም ክልሎች ለሚገኙ የህጋዊ ስነ-ልክ ባለሞያዎች ስልጠና ለመስጠትና ያለባቸውን የስታንዳርድ መለኪያ መሳሪያዎች በተወሰነ መልኩ ለማሟላት ፕሮጀክት ተቀርፆ ግዢውን በመፈፀም ለክልሎች ለማሰራጨት በዝግጅት መሆኑን እና ስለአጠቃላይ አፈፃፀማቸውም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት የሚያደርጉበትና በየግማሽ ዓመት በመገናኘት ለመገምገም በ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ መያዙን ገልጿል፡፡

117. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

118. ከምርትና አገልግሎት ጥራት ከማረጋገጥ አንፃር አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸውን የወጪና የገቢ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አሰራር ስርዓቱ ያልተጠናከረ በመሆኑ ምክንያት ብልሹ አሰራርና ተግባር ከማበረታታቱም በላይ የሸማቹን ጤንነት ደህንነት

አደጋ ላይ እየጣሉ፣ የንግዱን ማህበረሰብ ለፀረ-ውድድር እያጋለጡና በወጪ ንግድ እንቅስቃሴው በጥራት መጓደል ምክንያት የሀገር ገፅታ እያበላሹ መሆኑን ከንግድ ሚኒስቴር የማኔጅመንት ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

119. ንግድ ሚ/ር በደቡብ ክልል የሀገሪቱን የስነ ልክ ሥርዓት የዘረጋ መተግበሩን የሚቆጣጠር ቢሆንም ከመስከረም 2010 ዓ.ም ጀምሮ ቁጥጥር አድርጎ እንደማያወቅ፣ የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ሥራዎች በደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ተጠናክረው መሥራታቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን ከደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

120. በህጋዊ ስነ-ልክ ደንብና መመሪያን በተመለከተ ደንብና መመሪያ አለመኖሩን በተለይ በነዳጅ ዙሪያ ችግር መፍጠሩን፣ በንግድ ሚኒስቴር የሚደረግ ሞያዊ ድጋፍ እና የሚሰጥ ማቴሪያል በቂ አለመሆኑን ከትግራይ ክልል ንግድ፣ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

121. በደቡብ ክልል በመደበኛም ይሁን ድንገተኛ ምርመራ ወቅት ጉድለት የተገኘባቸውና የግብይት አገልግሎት ላይ የማይውሉ በመሆናቸው የተወረሱ ሚዛኖችን ለመውረስም ሆነ ለማስወገድ የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ በአሰራር ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑን፣ በክህሎት ላይ የተመሰረተና የተሟላ ፍተሻ ከማድረግ አንፃር በታችኛው መዋቅር የሰው ሀይል እጥረት እና የክህሎት ክፍተት መኖሩን ከደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

122. የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ዲያሜትራቸው ከ24 ሚ.ሜ በላይ የሆኑትን የአርማታ ብረቶች በላብራቶሪ መፈተሽ እንደማይችል በመግለፅ በሌሎች አማራጭ ላባራቶሪዎች ፍተሻ ለማካሄድ ጥረት ቢደረግም የተጠቀሰውን ውፍረት መፈተሽ የሚችሉ የሀገር ውስጥ ላብራቶሪዎች ማግኘት አለመቻሉን፣

123. ስለሆነም ውፍረታቸው ከ 24 ሚ.ሜ በላይ የሆኑ የአርማታ ብረቶች ያስመጡና በዚህ ምክንያት ሰነዶቻቸው በጉምሩክ ላልተበተነላቸው አስመጪ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ከላይ የተጠቀሰው ውፍረት የአርማታ ብረት የፍተሻ አገልግሎት መስተት እስከሚጀምር ድረስ ከዚህ በኋላ ለሚያስመጡት ምርቶች የሦስተኛ ወገን የጥራት ሰርተፊኬት እያቀረቡ እንዲስተናገዱ ለአሁኑ ግን ላስመጡት

የአርማታ ብረት በጉምሩክ በኩል ሰነዱ እንዲበተንላቸው የንግድ ሚኒስቴር የማኔጅመንት ኮሚቴ ወስኗል፡፡

124. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ሥራዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናክረው መሥራታቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡-

125. በትግራይ ክልል ቁጥጥር ( Inspection ) ከተደረገላቸው ሚዛኖች 491 ጥፋት የተገኘባቸው ሲሆኑ ማለትም ትክክለኛ ክብደት ማነፃፀሪያ የማይጠቀሙ 240፣ በተበላሸ ሚዛን የሚጠቀሙ 81፣ ክብደት ሊያዛቡ የሚችሉ ባዕድ ነገር የሚጨምሩ 58 እንዲሁም 112 የሚሆኑ የተለያየ ጥፋቶች የተገኙባቸው ሚዛኖች መኖራቸውን እና በእቅዱ መሰረት የቬሪፊኬሽን ስራ አለመሰራቱን ፣

126. በጋምቤላ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በ2009 ዓ.ም ሩብ ዓመት በ 10 ስጋ ቤቶች ላይ የሚዛን ጥናትና ቁጥጥር ተደርጎ 5 ስጋ ቤቶች ከግራም በታች እየሸጡ መገኘታቸው፣ በ20 አትክልት ቤቶች እና የችርቻሮ ቤቶች በተደረገው የሚዛን ጥናትና ቁጥጥር 10 አትክልት ቤቶች እና የችርቻሮ ቤቶች ከግራም በታች እየሸጡ መገኘታቸውን፣በ10 ወፍጮ ቤቶች ላይ  የሚዛን ጥናትና ቁጥጥር ተደርጎ 5 ወፍጮ ቤቶች ከ 1 ኪ.ግ ከ 10-100 ግራም ቀንሰው እየሸጡ መገኘታቸውን ፣

127. በደቡብ ክልል በተደረገ የሚዛን ምርመራ 424 ሚዛኖች እና 942 ክብደቶች ላይ ጉድለት የተገኘ ሲሆን በክልሉ ኮንታ ልዩ ወረዳ እስካሁን ምንም ዓይነት የሚዛን ምርመራ አለመከናወኑን፣

128. በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ 9 ቀበሌዎች እና 38 የገጠር ገበሬ ማህበሮችን አገልግሎት ለማዳረስ የስነ-ልክ መሳሪያዎች እጥረት ያለ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል የመስፈሪያ መሳሪያዎች ማነፃፀሪያ በበቂ ሁኔታ ያለማሟላት በወረዳና በከተሞች ስራው በተፈለገው ፍጥነት አለመሄዱን፣ የሥነ-ልክ ባለሞያዎች በአንዳንድ ወረዳዎች ያለመሟላት ችግሮች መኖሩን ፣ በአማራ ክልል በመለኪያ መሳሪያዎች ቬሪፊኬሽንና ኢንስፔክሽን ስራ ከተሰራባቸው የመለኪያ መሳሪያዎቹ ውስጥ 6017 በሚሆኑት ላይ ጉድለት የተገኘ መሆኑን፣

129. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አብዛኛውን ኖዝሎች ላይ የሚሰጡት የነዳጅ መጠን ከ20 ሊትር መጠን ላይ ከ 50 ሚሊ ሊትር በታች ወርደው መታየታቸው፣ በዋናነት በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ካዛንችስ ሱፐር ማርኬት ላይ ከ 200 ሚሊ ሊትር በታች በብዛት (ከአንድ ኖዝል በስተቀር) መታየቱን፣ በንግድ ሚኒስቴር ፕሉፕ የተሰሩ ማደያዎች ላይ ክፍተት በስፋት መታየቱን፣ በልዩነት ቦሌ የተባበሩት ላይ ብቻ 160 ሚሊ ሊትር ነጭ ጋዝ እንዲሁም አንድ የቢንዚን ኖብል ላይ 140 ሊትር ተጨማሪ በየ 20 ሊትር ላይ እየሰጠ መታየቱ ፣

130. በጉለሌ ክፍለ ከተማ ዊንጌት አደባባይ ኖክ ቤንዚን ማደያ ላይ በየ 20 ሊትር ሁሉም ማሽኖች ከ 90 እስከ 460 ሚሊ ሊትር በማጉደል አገልግሎት ሲሰጡ እንደነበርና ይህም የተሰራው በንግድ ሚኒስቴር ፕሉፕ መሆኑን፣በየካ ክፍለ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ ኖክ እነዲሁም ወሰን ግሮሰሪ ኦይል ሊቢያ በ 20 ሊትር መጠን ውስጥ ተጨማሪ 190 ሚሊ ሊትርና 200 ሚሊ ሊትር ጉድለት አገልግሎት እንደሚሰጡ፣ ዓመታዊ የነዳጅ ሜትሮች ምርመራ ወቅቱን ጠብቆ ባለመሰራቱና ማሽኖቹ በተፈዋሮ ቶሎ የሚበላሹና ለዚህም ተከታታይ ክትትል እንደሚያስፈልገው ፣

ከክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

131. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልሎች የሚካሄዱ የመለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን በማስተባበር የማነጻጸሪያ መሣሪያዎቻቸውን ካሊብሬት እንዲያስደርጉ ማድረጉንና አፈጻጸማቸውን መከታተሉን በተመለከተ፡-

132. በደቡብ ክልል የሚካሄዱ የመለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን በማስተባበር የማነጻጸሪያ መሣሪያዎቻቸውን ካሊብሬት እንዲያስደርጉ የሚያደርግና አፈጻጸማቸውን የሚከታተል መሆኑን የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች የገለፁ ቢሆንም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

133. በትግራይ ክልል የነዳጅ ማደያዎች ካኖፒ (ጥላ) ባለመኖሩ ካላብሬት ማድረጊያ ቁጥሮች እንደማይሰሩ ፣ በክልሉ ካለው 112 የአንድ አገልግሎት ብዛት ሲታይ 23 የሚዛን ማነፃፀሪያ ክብደቶች ብቻ መኖራቸውን እንዲሁም ግራማቸው የተጓደሉ በመሆናቸው በሚዛን ማጭበርበር በሚገባ አለመሰራቱን ፣

134. እንዲሁም የትግራይ ክልል ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ለንግድ ሚኒስቴር በፃፉት ደብዳቤ በሚዛንና የሚዛን ማነፃፀሪያ ክብደቶችን ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ በደረጃ መዳቢዎች በ1995 ዓ.ም የወጣው አዋጅ መሆኑ፣ ይህ አዋጅ በሰራር ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በሚፈታ መልኩ ተዘጋጅቶ ሊፀድቅ ነው እየተባለ ከአራት ዓመት በላይ ማስቆጠሩን፣

135. በዚሁም መሰረት በስራ ላይ ያሉ ያገለገሉ፣ ያረጁ፣ የተበላሹ ሚዛንና የሚዛን ማነፃፀሪያ ክብደቶች ግልፅ የሆነ አወጋገድና እርምጃ አወሳሰድ የሚገልፅ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ስለሌለው በተደጋጋሚ በስልክ ለንግድ ሚኒስቴር የነበሩ አመራሮችና ሰራተኞች ቢጠይቁም አዋጁ ሊፀድቅ ነው የሚል መልስ ብቻ እንጂ እስካሁን መፍትሔ የሚሰጣቸው አካል አለማግኘታቸውን፣

136. ጥያቄዎቹ በጊዜ መፍትሄ ባለማግኘታቸው የሚፈለገውን ስራ ለመስራት አለመቻሉን፣ በተጨማሪም በሚዛን ተቆጣጣሪ ሰራተኞች የተበላሹ ሚዛኖችን በሚዛን ማነፃፀሪያ ክብደቶች ሰብስበው ከንግድ ድርጅቶች ወስደው በሚያስወግዱበት ጊዜ ነጋዴው በየትኛው አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ነው ንብረታችንን የምታስወግዱት የሚል ጥያቄ እና ክስ እየመሰረቱ እንደሚገኝ፣

137. ስለሆነም በሚዛንና የሚዛን ማነፃፀሪያ ክብደቶች የተበላሹ ግልፅ የሆነ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ስለሌለ በስራውና በሰራተኛው ከፍተኛ የሆነ መጉላላትና ተፅእኖ እየፈጠረ ስለሆነ አስቸኳይ መፍትሄ እንዲሰጣቸው መጠየቃቸውን፣

138. በጋምቤላ ክልል አዲስ የሚተከሉ የነዳጅ ማሽኖች ካሊብሬት ማድረግና በመለኪያ መሳሪያ በየወሩ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ በባለሞያ እጥረት ምክንያት ስራው አለመከናወኑን፣ የተሰጣቸው ሚዛን ጥቂት በመሆኑ ምክንያት በየወረዳዎቹ አለመዳረሱን ፣ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል በነዳጅ ላይ ክትትል ለማድረግ በማደያው ባሉ ማሽኖች ላይ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው፣ የዳቦና የወርቅ የልኬት መሳሪያዎች አለመኖሩን፣

139. በደቡብ ክልል በእያንዳንዱ ወረዳና ክፍለ ከተማ ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ የመመርመሪያ መሳሪያ እጥረት መኖሩን፣ የምድር የመመርመሪያ መሳሪያውን ከቦታ ቦታ ይዞ ለመንቀሳቀስ የማይመች መሆኑንና በማንቀሳቀሱም ሂደት በርካታ የአያያዝ ጉድለቶች መታየታቸውን፣ በክህሎት ላይ የተመሰረተና የተሟላ ፍተሻ ከማድረግ

ከማድረግ አንፃር በታችኛው መዋቅር የሰው ሀይል እጥረትና የክህሎት ክፍተት መኖሩን፣

140. እንዲሁም በመደበኛም ይሁን ድንገተኛ ምርመራ ወቅት ጉድለት የተገኘባቸውና የግብይት አገልግሎት ላይ የማይውሉ በመሆናቸው የተወረሱ ሚዛኖችን ለመውረስም ሆነ ለማስወገድ የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ በአሰራር ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑን፣ አዲስ የሚከፈቱ ማደያዎችን ወደ ስራ ለማስገባትም ሆነ ነባር ማደያዎችን መደበኛ ዓመታዊ ምርመራ ለማድረግ ለእሽጋ የሚጠቅመው መጭመቂያ/ ፕላምፕ/ እና ሌሎች ስራውን ለማከናወን የሚረዱ መሳሪያዎችን ንግድ ሚኒስቴር ሊሰጣቸው ባለመቻሉ ሙሉ በሙሉ የመደበኛውን ምርመራ ስራ ለመስራት መቸገራቸውን ፣

141. በአማራ ክልል የመለኪያ መሳሪያዎች ስታንዳርድ በወቅቱ ካሊብሬት አለመደረጋቸውን፣ የፈሳሽ ልኬታዎችን ለመለካትና ከዓለም አቀፍ የልኬት ስታንዳርዶች ጋር ለማነፃፀር የማነፃፀሪያ ስታንዳርዶች አለመኖራቸውን ፣ አብዛኛው የቬሪፊኬሽን ስራ ወደ ዞን የተሰጠ ስለሆነ በትጋት አለመሰራቱን ፣ በነዳጅ ማደያ ቬሪፊኬሽን የባለሞያዎች የክህሎት ክፍተት መኖሩን፣

ከክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

142. በተጨማሪም የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ፍተሻ የሚደረግበት የአምፖል ፓራሜትርን በሚመለከት የብርሃን መጠኑን ለመፈተሽ የሚጠቀሙበት ማሽን የካሊብሬሽን ጊዜ ያለፈበት በመሆኑ ግዢ እስኪፈፀም ድረስ በዚህ ፓራሜትር መፈተሽ እንደማይችሉ በደብዳቤ መግለፃቸውን፣ በዚህም መሰረት የአምፖሉ የብርሃን ደረጃ መስፈርት ማሟላቱን ማረጋገጥ ፓራሜትር በጣም ወሳኝ ከመሆኑ የተነሳ በዚህ ፓራሜትር ያልተፈተሸ አምፖል ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ መፍቀድ አስቸጋሪ እንደሆነ ግንዛቤ መወሰዱን፣

143. በመሆኑም የገቢ እና ወጪ እቃዎች ምርት ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ከኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ውይይት ለጊዜው የመፈተሻ ማሽኑ የካሊብሬሽን ጊዜው ያለፈበት ቢሆንም የአምፖሎቹ ብርሃን መጠን ሳየፈተሽ ከማስገባት ይልቅ በዚህ ማሽን ፈትሾ ማስገባቱ የተሻለ እንደሆነ መግባባት ላይ የተደረሰ መሆኑ ተገልፆ የተደረሰበት መግባባት ተግባራዊ እንዲደረግ የማኔጅመንት ኮሚቴው መወሰኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

144. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሕጋዊ ስነ-ልክ አተገባበር የሚከታተልበት በሁለት መንገድ ሲሆን አንደኛዉ በየሩብ ዓመቱ በሚደረገዉ የክልል መድረኮች ላይ ግምገማ በማካሄድ፣ ሁለተኛዉ በአካል ክልሎች ጋር በመገኘት ከክልሎች ጋር በመሆን በጋራ የሱፐርቪዥን ስራዎች የሚያከናዉን መሆኑን፣ ክልሎች የመቆጣጠሪያ ስታንዳርድ መሣሪያዎቻቸዉን በዓመት አንድ ጊዜ ካልብሬት ማስደረግ እንዳለባቸዉ በሚደረጉት ግንኙነቶች የሚገለጽ ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱም ካልብሬት ስለማድረጋቸዉ የሚከታተለዉ በሱፐርቪዥን እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

145. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ታህሳስ 11 ቀን 2010 ዓ.ም ባደረገው የማኔጅመንት ቃለ-ጉባኤ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸውን የወጪና የገቢ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አሰራር ስርዓቱ ያልተጠናከረ በመሆኑ ምክንያት ብልሹ አሰራርና ተግባር ከማበረታታቱም በላይ የሸማቹን ጤንነት ደህንነት አደጋ ላይ እየጣሉ ፣ የንግዱን ማህበረሰብ ለፀረ-ውድድር እያጋለጡና በወጪ ንግድ እንቅስቃሴው በጥራት መጓደል ምክንያት የሀገር ገፅታ እያበላሹ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

**የመለኪያ መሣሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ <u>መሆኑን ማረጋገጡን በተመለከተ፣</u>**

146. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

147. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጭ የሚገቡ የመለኪያ መሳሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑ የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ማረጋገጫ ቬሪፋይ ሳይደረጉ በጊዜያዊ መልቀቂያ የሚለቀቁና በክልሎችም የመለኪያ መሳሪያዎቹ ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን የማይረጋገጥ መሆኑ፣

148. ሁሉም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የመለኪያ መሳሪያዎች አስመጪዎች የትክክለኛነት ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው ለሚ/ር መ/ቤቱ የአገልግሎት ጥያቄ በደብዳቤ ቢያቀርቡም ሚ/ር መ/ቤቱ ከ 39 አመት በፊት ይሰራበት በነበረው አሰራር የመለኪያ መሳሪያዎቹን ትክክለኛነት ሳያረጋግጥ በህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 431/1968 ዓ.ም የሚዛንና መስፈሪያ ደንብ ቁጥር 5 መሰረት የትክክለኛነት ማረጋገጫ ሳይሰጣቸው በውዴታ ግዴታ እንዲለቀቁ እንደሚደረግ ተገኝቶ ነበር፡፡

149. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሸማቹን ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር የመለኪያ መሳሪያዎች ወደ ከገበያ ከመግባታቸው በፊት በፌደራልና በክልል ንግድ ቢሮዎች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ሊያረጋግጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

150. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በጊዜያዊ መልቀቂያ እንዲለቀቁ የሚደረግበት አሰራር ከመጋቢት 2008 ዓመት ጀምሮ የቀረ መሆኑን ገልጿል፡፡

151. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

152. የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች የመለኪያ መሣሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን የሚያረጋግጥ መሆኑን ቢገልፅም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

153. ከንግድ ሚኒስቴር የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለመረዳት እንደተቻለው ከፍተኛ የመለካት አቅም ያላቸው ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ሚዛኖች በኤርፖርት ጉምሩክ መፈተሻ ጣቢያ የማነፃፀሪያ ክብደቶችን ጉምሩክ ግቢ ማስገባት ባለመቻሉ ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ሁኔታ መፍጠሩ ታውቋል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገልጋዮች ቬሪፊኬሽን ለማስደረግ የክብደት ማነፃፀሪያዎች ወስደው እንዳያዘገዩ ውል በማስገባት መሣሪያዎቹ በወቅቱ እንዲመልሱ ማድረጉን <u>በተመለከተ፣</u>**

154. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

155. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገልጋዮች የተሸጋጋሪ ሚዛን (Standard Weight) ክብደት ማነፃፀሪያ ቬሪቪኬሽን ለማስደረግ ወስደው እንዳይዘገዩና በወቅቱ እንዲመልሱ ግዴታቸውን የሚያሳውቅበት አሰራር ስለሌለው አንዳንድ ተገልጋዮች መሳሪያዎቹን ከወሰዱ በኋላ ለቀጣዩ ተገልጋይ ያለማስረከብና የስራ መጓተት የሚፈጠርበት ሁኔታ መኖርና ችግሩን ለማስተካከልም የተወሰደ እርምጃ እንደሌለ፣ እንዲሁም በክልሎች የሚገኙ ዞንና ወረዳዎች የማነጻጸሪያ መሳሪያዎችን ስለማይወስዱ ቢሮ ድረስ

በመምጣት ካሌቢሬት የሚያስደረጉ በመሆኑ በወቅቱ ካሊቤሬት እንደማያደርጉ ተገኝቶ ነበር፡፡

156. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገልጋዮች ቬሪፋይ ለማስደረግ የክብደት ማነጻጸሪያ መሳሪያዎችን ወስደው ከተጠቀሙበት በኋላ እንዳያዘገዩና በወቅቱ እንዲመልሱ ውል አስገብቶ በውሉ መሰረት ተከታትሎ መሳሪያዎቹ እንዲመልሱ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

157. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ከሀምሌ 2008 ዓ.ም ጀምሮ የተሸጋጋሪ ሚዛን ትክክለኛነት ማረጋገጫ የሆኑ ስታንዳርድ የክብደት ማነፃፀሪያዎች /standard check weihts/ ተገልጋዮች የሚረካከቡት ማስረከቢያና የውዴታ ግዴታ የሚገቡበት ቅፅ በማዘጋጀት ተገልጋዮች እንዲረካከቡ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

158. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

159. ንግድ ሚ/ር ተገልጋዮች ቬሪፊኬሽን ለማስደረግ የክብደት ማነፃፀሪያዎች ወስደው እንዳያዘገዩ ውል አስገብቶ መሣሪያዎቹ በወቅቱ እንዲመልሱ እንደሚያደርግ የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የሚነለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች የገለፁ ቢሆንም ማስረጃው ለኦዲትቡድኑ አልቀረበም፡፡

160. እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገልጋዮች ቬሪፊኬሽን ለማስደረግ የክብደት ማነፃፀሪያዎች ወስደው እንዳያዘገዩ ውል አስገብቶ መሣሪያዎቹ እየሰጠ እንደሆነ ከአማራ፣ ከአዲስ አበባ፣ ከአፋር ክልሎች ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ጋር ካደረገው የጊዜያዊ የንብረት ማረካከቢያ ቅፅ ውል ለመረዳት የተቻለ ቢሆንም መሣሪያዎቹ በወቅቱ ስለመመለሳቸው የኦዲት ቡድኑ ማስረጃ አላገኘም፡፡

**የአውቶ ቦቴ የቬሪፊኬሽን የአገልግሎት ክፍያ ተመን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር መሆኑን ፣ የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር ( ቦቴ) የቬርፊኬሽን <u>ሰርተፊኬት የሚሰጥና ተግባራዊ መደረጉን ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣</u>**

161. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

162. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ ቬርፌኬሽን የአገልግሎት ክፍያ ዋጋው በ1966 ዓ.ም የሚዛንና መስፈሪያ ማስከፈያ ደንብ ቁጥር 431 መሰረት የወጣ በመሆኑ አሁን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ተመጣጣኝ እንዲሆን አለመደረጉ ተገኝቶ ነበር፡፡

163. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ የቬርፌኬሽን የአገልግሎት ክፍያን አሁን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር ወቅታዊ በማድረግ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ሊያስከፍል፣ የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር (ቦቴ) የመለኪያ መሳሪያ ከተገጠመለት በኋላ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ መሆኑን በማረጋገጥ ቬሪፋይ አድርጎ የሚሰጠው ሰርተፊኬት የተቀመጠለትን ጊዜ ጠብቆ የሚሰጠው መሆኑን ሊያረጋግጥ እና በሀሰተኛ ሰርተፊኬት አስመስለው በሚሰሩት ላይ እገዳ ሊያደርግና በህግ አግባብ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

164. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በ1996 ዓ.ም የወጣው የአውቶ ቦቴ ቬሪፌኬሽን የክፍያ ተመንና ሌሎች በህጋዊ ስነ-ልክና በገቢና ወጪ እቃዎች ጥራት ቁጥጥር የኢንስፔክሽን ተመኖችን ለማሻሻል የተዘጋጀውን ረቂቅ ደንብ በማፅደቅ ወደ ስራ እንደሚገባ፣ የሐሰተኛ ሰርተፊኬት በማቅረብ ሲገለገሉ በተገኙት ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንደሚወሰድ በ2009 ዓ.ም በእቅድ መያዙን ገልጿል፡፡

165. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

166. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ ቬርፌኬሽን የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ቀደም እንደነበረው ዋጋው በ1966 ዓ.ም የሚዛንና መስፈሪያ ማስከፈያ ደንብ ቁጥር 431 መሰረት የወጣ መሆኑን እና የዋጋ ማሻሻያ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

167. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር (ቦቴ) ይዘት የመለኪያ መሳሪያ ከተገጠመለት በኋላ የመሳሪያውን ትክክለኛነት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ መሆኑን በማረጋገጥ ለሶስት ዓመት የሚያገለግል የቬርፌኬሽን ሰርተፊኬት መስጠቱንና በተሰጠው መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፡-

168. የህጋዊ ስነ-ልክ የአውቶ ቦቴ የውሃ ታንከሮች ቀበራ ችግር ያልተፈታ መሆኑን፣ አሮጌው የውሃ ማጠራቀሚያ ባለመጠገኑ ውሃ እየሰረገ የውሃ እጥረት ማስከተሉንና አገልግሎት ፈላጊዎች ቶሎ ምላሽ አለማግኘታቸውን ከንግድ ሚኒስቴር ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

169. በትግራይ ክልል ለብዙ ዓመታት በስራ ላይ የነበሩት የነዳጅ መደያዎች ማሽኖች ያረጁና የተበላሹ መሆናቸውን እና ለእያንዳንዱ ከተሞችና ወረዳዎች የነዳጅ መቆጣጠሪያዎች ፕሮቮሮችና መጨፍለቂያዎች ባለመኖሩ በቅርበትና በፍጥነት አገልግሎት መስጠት አለመቻሉን ከትግራይ ክልል ንግድ ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

170. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው የአዉቶ ቦቴ ሽሪፊኬሽን የአስገዳጅ የስነ ልክ አዋጅ በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ በጠቅላይ አቃቤ ህግ ከታየ በኋላ ለማጽደቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ከተላከ ሁለት ወራት ያለፈው ቢሆንም በወቅቱ ባለመፅደቁ እየተጠበቀ እንደሚገኝ፣ የቀረበዉ የሕጋዊ ስነ-ልክ አዋጅ በቅድሚያ መጽደቅ ያለበት በመሆኑና በአዋጅ ላይ ደንብና መመሪያ በክፍያ ዙሪያ አዋጁ ከጸደቀ በኋላ በቀጣይነት የክፍያ ተመን ማሻሻያ ደንቡ እንደሚጽድቅ ገልፀዋል፡፡

171. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ እንደዚሁ የዋጋ ማሻሻያ ለማድረግ የሚወጣው ደንብ በረቂቅ ደረጃ እንደሆነ መግለፃቸው የሚታወቅ ነው፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ፣ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከተገልጋዮች ጋር <u>ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ያለው መሆኑን በተመለከተ፣</u>**

172. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

173. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በሌሎች አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ መደበኛ የሆነ ጉባኤ አዘጋጅቶ በመጥራት እያወያየ አለመሆኑ፣

174. በኦዲቱ በናሙና በታዩት ቅ/ጽ/ ቤቶች የአዲስ አበባ ፣ አዳማ፣ በኮሜት ተ/ጽ/ቤት፣ የአዋሣ፣ የሞያሌ፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሌሎች አስፈጽሚ መ/ቤቶች የሚሠራባቸው

አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ከባለድርሻ አካላት ጋር በሚፈለገው መልኩ በቅንጅት የማይሰሩና እንዲሁም በሚሰሩ ስራዎች በአሰራር ላይ ባሉ ችግሮችና መፍትሄዎች አፈጻጸም ላይ ለማወያየት መደበኛ የሆና ተከታታይ ጉባኤ አለመደረጉ፣

175. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው የክልል ንግድ ቢሮዎች የሀዋሳ ፣ የአዲስ አበባ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎችና የኦሮሚያ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ሚ/ር መ/ቤቱ በህጋዊ ስነልክ አተገባበር ዙሪያ ወጥነት ያለው ቋሚ የሆነ የመወያያ መድረክ በማዘጋጀት ተግባራዊ ባለማድረጉ እስከ ወረዳ ድረስ በመውረድ ሥራው የተፈለገውን ያህል አለመሠራቱ፣

176. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የገቢና ወጪ የንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃውን መስፈርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በትብብር እንዲሠራ ስልጣን ቢሰጠውም ከሁሉም አስፈጻሚ አካላት ጋር በተሟላ መልኩ በትብብር እየሠራ አለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

177. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሌሎች አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገብሩ ሊያደርግና በአፈጻጸም ላይ መደበኛ የሆነ ጉባኤ ሊያዘጋጅና ሊያወያይ፣ የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎች አስፈላጊውን የደረጃ መስፈርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር እንዳይገቡ ወይም እንዳይወጡ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካለት ጋር ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን ተከታታይነት ያለውን የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ግንዛቤ በማስጨበትና አስፈላጊ የሆኑ ወቅታዊ መረጃዎችን በመስጠትና በመለዋወጥ፣

178. እንዲሁም የአንድ አከባቢ አገልግሎት ለተገልጋዩ በመስጠት በትብብር ሊሰራና እንዲሁም ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያስገቡና ከሚያስወጡ ተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚነሱ ችግሮች በተደጋጋሚ እንዳይከሰቱና ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ በጋራ ለመፍታት በየስድስት ወሩ መደበኛ የውይይት መድረክ ሊያዘጋጅና ወቅቱን ጠብቆ ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

179. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የቅንጅታዊ አሰራር የተጠናከረ እንዲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ መደበኛ የሆነ የውይይት መድረክ በዓመት አንድ ጊዜ ለማድረግ በ2009 ዓ.ም በእቅድ መያዙን ገልጿል፡፡

180. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

181. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሌሎች አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገብሩ ማድረጉንና በአፈጻጸም ላይ የሚያወያይ መደበኛ ጉባኤ መጥራቱን በተመለከተ፡-

182. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአፈጻጸም ላይ የሚያወያይ መደበኛ ጉባኤ በ 2009 ዓ.ም አንድ ጊዜ ብቻ ማደረጉን ፣ በ2009 ዓ.ም በንግድ ሚ/ር ዋናው መ/ቤት የተካሄደ ጉባዔ መኖሩን፣ በዓመት ሁለት ጊዜ በአፈጻጸም ላይ የሚያወያይ መደበኛ ጉባኤ የሚደረግ መሆኑን እና በቅ/ፅ/ቤት ደረጃ ግን እንደማይካሄድ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሌሎች አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገብሩ በአፈጻጸም ላይ የሚያወያይ መደበኛ ጉባኤ ጠርቷቸው እንደማያውቅ ከሚመለከታችው የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

183. ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ቅ/ፅ/ቤቱ እቃ ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያስገቡና ከሀገር ከሚያስወጡ ተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችልና በአፈጻጸም ላይ የሚያወያይ መደበኛ ጉባኤ ጠርቷቸው እንደማያውቅ የአዳማ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

184. በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሌሎች አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገብሩ እንደማያደርግ ፣ በአፈጻጸም ላይ የሚያወያይ መደበኛ ጉባኤ እንደማይደረግ ፣ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ንግድ ሚ/ር በሃዋሳ ቅርንጫፍ እንዳለው የማያውቁ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

185. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀዋሳ ተስማሚነት ምዘና ድርጅትን አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገብሩ በአፈጻጸም ላይ የሚያወያይ መደበኛ ጉባኤ አዘጋጅቶ ጠርቷቸው

እንደማያውቅ የሀዋሳ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

186. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በትብብር የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ፡-

187. የሞጆ ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ፣ ከገቢዎች እና ኩምሩክ ባለስልጣን ጋር በትብብር እንደሚሰራ የገለፁ ሲሆን የሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር ደብዳቤ ከመፃፃፍ ያለፈ ሌላ የሥራ ግኑኙነት የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

188. እንዲሁም በንግድ ሚኒስቴር የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የተውጣጣ ኮማንድ ፖስት መኖሩን እና በኮማንድ ፖስቱ አማካኝነት በትብብር የሚሰሩ መሆኑን የገለፁ ሲሆን የአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ከንግድ ሚ/ር ጋር በየጊዜው አለመገናኘታቸውን ፣ ችግሮችን እየፈቱ አለመሆኑን እና በቅንጅት አለመስራታቸውን ገልፀዋል፡፡

189. በተጨማሪም የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በቅንጅት እንደማይሰራ የገለፁ ሲሆን የሀዋሳ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ከሀዋሳ ንግድ ሚ/ር ቅ/ፅ/ቤት ጋር የላብራቶሪ ፍተሻን በተመለከተ በትብብር እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

190. የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በትብብር እንደሚሰራ የገለፁ ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከብቃት አረጋጋጭና ከሌሎች የሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በሚፈለገው ደረጃ መቀናጀት አለመቻሉን ከንግድ ሚኒስቴር የማኔጅምንት ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

191. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያሰገቡና ከሚያሰወጡ ተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ቋሚ የምክክር መድረኮች ማዘጋጀቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-

192. የሞጆ ቅ/ፅ/ቤት እና የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የሥራ ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ እቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያሰገቡና ከሚያሰወጡ ተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ቋሚ የምክክር መድረኮች እንደሚዘጋጁ የገለፁ ቢሆንም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

193. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያሰገቡና ከሚያሰወጡ ተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ቋሚ የምክክር መድረኮች አለመኖራቸውን፣ ውይይትም ተደርጎ እንደማያውቅ፣ ከተገልጋዮች ጋር ቋሚ የመወያያ መድረክ ባለመዘጋጀቱና ችግሮች ባለመፈታታቸውም ባለጉዳዮች ለዲሚሬጅ (የመጋዘን ወጪ) እንዲጨምር፣ እንዲሁም እቃ ማስቀመጫ ቦታዎች እንዲጣበብ ማድረጉን የሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

194. እንዲሁም ከአዳማ እና ከሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያሰገቡና ከሚያሰወጡ ተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ቋሚ የምክክር መድረኮች እንደማይዘጋጁ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ከተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት በየ6 ወሩ ቋሚ የምክክር መድረኮች ያዘጋጀ መሆኑን ፣ ከክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ባለሙያዎች ጋር በየሩብ ዓመቱ ውይይት ማድረጉንና በየስድስት ወሩ ግምገማ ማካሄዱን <u>በተመለከተ፣</u>**

195. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

196. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቃዎችን ከሀገር ውስጥ የሚያስገቡና ከሀገር ውጭ የሚልኩ ተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በየ6 ወሩ ቋሚ የግንኑኝነት መድረኮች ሊያዘጋጅና ተግባራዊ እንደሚያደርግ ቢገልጽም ከ2005-2007 በጀት ዓመት መደበኛ የሆነ የግንኙነት መድረክ እንደሌላቸው ፣

197. ነገር ግን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ፣ ከብሔራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት፣ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣ ከኢትዮጵያ የኢነርጅ ባለሥልጣን፣ ከመድኃኒትና ምግብና ቁጥጥር ባለሥልጣን እና ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር የጋራ መድረክ ተዘጋጅቶ ውይይት እንደሚያደርጉ ቢገልጹም በቃለ ጉባኤ ያልተደገፈና ማስረጃው የሌለው መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

198. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ንግድና ኢንዱስተሪ ቢሮ የህጋዊ ስነ ልክ ባለሙያዎች ጋር ስራው በትክክል እየተከናወነ ስለመሆኑና ክልሎች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት ሃላፊነታቸውን እየተወጡና ተግባራዊ እያደረጉ ስለመሆኑ በአፈጻጸሙ ዙሪያ በየሩብ ዓመቱ ውይይት ሊያደርግ እና በአጠቃላይ በስራዎቹ ላይ በሚታዩ ጉዳዮች በየስድስት ወሩ አንድ ጊዜ ግምገማ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

199. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በህጋዊ ስነ-ልክ አፈፃፀም ዙሪያ ከክልሎች ጋር በየግማሽ ዓመቱ ግምገማ በማከናወን ያሉትን ክፍተቶች በመወያየት ለመቅረፍ በ2009 ዓ.ም በእቅድ መያዙን ገልጿል፡፡

200. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

201. የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የሥራ ሃላፊዎች ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር በሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥራ አፈጻጸም ዙሪያ ውይይት የሚያደርግና የሩብና ዓመታዊ ሪፖርቶችን በጋራ የሚገመግሙ መሆኑን ቢገልፁም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

202. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክልሎች በሕጋዊ ስነ-ልክ አፈጻጸም ዙሪያ በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት በስልክ ግንኙነት በተጨማሪ ሪፖርት እንዲያደርጉ የሚከታተል እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

203. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎችን ስለመከታተሉ የሚያሳይ ማስረጃ ለክትትል ኦዲት ቡድኑ አላቀረበም፡፡

**ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዘ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይይት ያደረገና መፍትሄ ያስቀመጠ መሆኑን በተመለከተ፣**

204. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

205. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዘ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይይት በማድረግ መፍትሄ ማስቀመጥ እንዳለበት በሁለቱ መ/ቤቶች የመግባቢያ ሰነድ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ውይትት በማድረግ የመፍትሄ እርምጃ አለማስቀመጡን፣

206. በኦዲቱ በናሙና በታዩ ቅ/ጽ/ቤቶች የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት መዘግየት ጋር በተያያዘ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር የውጤት መዘግየት በተመለከተ በተደጋጋሚ ውይይት ቢያደርግም ችግሩ በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚስተዋል መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

207. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከላብረቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዙ ከተገልጋዮች ለሚነሱ ጉዳዮች ቅሬታ እንዳያሳድር ትኩረት በመስጠት ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይይት ሊያደርግና የሚነሱ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ ሊያስቀምጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

208. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ላይ ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዘ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይትት ስለማድረግና መፍትሄ ስለማስቀመጥ አላካተተም፡፡

209. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

210. ከውጤት መዘግየት ጋር በተያያዘ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይትት የሚደረግ ቢሆንም የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ያለው ላብራቶሪ አንድ ብቻ በመሆኑ ውጤቱ ቢዘገይም ከመጠበቅ ውጪ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን በንግድ ሚኒስቴር የሞጆ ተወካይ ቅ/ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

211. በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የላብራቶሪ ውጤት መዘግየት በሚፈጠርበት ወቅት በስልክ እንዲሁም በአካል በመሄድ ከአዳማ ተስማሚነትና ምዘና ድርጅት ጋር ውይይት

የሚያደርጉ መሆኑን የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የስራ ሃላፊዎች የገለፁ ሲሆን የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዘ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከሀዋሳ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር በቃል ደረጃ ውይይት በማድረግ መፍትሄ ቢቀመጥም ችግሩ ተመልሶ እንደሚፈጠር ገልፀዋል፡፡

212. የአዳማ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሥራ ሃላፊዎች በበኩላቸው ከአዳማ ንግድ ሚ/ር ቅ/ፅ/ቤት ጋር ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት በተያያዘ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ቋሚ የሆነ ውይይት የማያደርግ ቢሆንም በቃል በመነጋገር ችግሮችን እንደሚቀርፉ የገለፁ ሲሆን የሀዋሳ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሥራ ሃላፊዎች ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዘ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይትት እንደማያደርግና ለችግሮች መፍትሄ እንደማያስቀምጥ ገልፀዋል፡፡

213. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በዋናነት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን የምርት ናሙና በላብራቶሪ ፍተሻ የሚያደርገዉ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የላብራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት እየሰጠበት የሚገኝበትን የአዲስ አበባ ዋናዉ መስሪያ ቤት ሲሆን ሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወደ ማዕከል ናሙና ልከዉ የሚያስፈትሹ መሆኑን፣

214. ሆኖም ግን የቁጥጥር ስራዉ በባህሪዉ ጊዜ የማይሰጥና አፋጣኝ ምልሻ መስጠት የሚያስገድድ በመሆኑ የመደበኛ የመወያያ ጊዜ ሳይጠበቅ በየጊዜዉ ከድርጅቱ ጋር በመገናኘት የመፍትሔ እርምጃዎች እየተሰጠ መሆኑን ፣

215. የንግድ አሰራርና የሪጉላቶሪ ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ከገቢና ወጪ እቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክተር ጋር በጋራ በተስማሚነት ምዘና ድርጅት በመገኘት የላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት የሚፋጠንበትን ሁኔታ በመነጋገር መፍትሄ ለመስጠት የተሰራ መሆኑን፣

216. በሶላር እቃዎች ላይ የተፈጠረውን ቅሬታ ለመፍታት ከድርጅቱ ጋር በቅርበት እየተሰራ እንደሚገኝ፣ የቀድሞ ጭነት ኢኒስፔክሽን ሰርተፊኬት አሰራር ማንዋልን (PVOC:-Pre-Export Verification of Conformity) ከድርጅቱ ሀላፊዎች ጋር በጋራና በመተባበር እየተሰራ እንደሆነ ፣ በአጠቃላይ የቁጥጥር ስራውን የተጠናከረ ለማድረግና አገልግሎት አሰጣጣችንን የተቀላጠፈ ለማድረግ ከሁሉም ባለድርሻ አካላትና ተቋማት ጋር በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

217. ይሁን እንጂ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት በሀገር ደረጃ ያለው ላብራቶሪ አንድ ብቻ በመሆኑ የላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት መዘግየት ያልተፈታ መሆኑን ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ታውቋል፡፡

**ናሙናዎች መረጃ በመረጃ ቋት ተመዝግቦ እንዲያዝ መደረጉን ፣ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለቅ/ጽ/ቤቶችና ለተገልጋዮች እንዲሰራጭ ማድረጉንና ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር መረጃ የሚለዋወጥና መሆኑን በተመለከተ፣**

218. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

219. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሥሩ የሚገኙ በናሙና በታዩት በአዲስ አበባ፣ በኮሜት፣ በሞጆ፣ በአዳማ፣ በሀዋሳ እና በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤቶች የናሙና ተረካቢ ሠራተኛ ባለመኖሩ የናሙናዎች መረጃ በመረጃ ቋት ተመዝግቦ እንዲያዝ አለመደረጉን፣

220. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለስራ አጋዥ የሆኑ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃዎችን በሚፈለገው ደረጃ በማሰብሰብና በማደራጀት ወጥ በሆነ መልኩ ወቅቱን ጠብቆ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ለክልሎች እንዲሰራጩ አለማድረጉ ተገኝቶ ነበር፡፡

221. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች መደበኛ የሆነ የናሙና ተረካቢ ሠራተኛ በመመደብ የናሙናዎች መረጃ በጥንቃቄ በመረጃ ቋት ተመዝግቦ እንዲያዙ ሊያደርግ፣ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ለተገልጋዮች ለስራ አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን በመተንተንና በማደራጀት ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖር ወቅቱን ጠብቆ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ሊያሰራጭና ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር አስፈላጊ የሆኑ መረጃ ሊለዋወጥና ወርሀዊ ወይም የሩብ አመት ሪፖርቶችን በጋራ ሊገመግም እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

222. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በቅ/ፅ/ቤቶች የሚታየውን የሰው ሀይል እጥረት ለማሟላት በ2009 ዓ.ም በእቅድ መያዙን፣ ከግንቦት 2008 ዓ.ም ጀምሮ ወቅታዊ መረጃዎች በ IT በመጠቀም ለሁሉም ቅ/ፅ/ቤት የሚሰራጩበት አሰራር መፈጠሩን እና ከኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር መረጃ የመለዋወጥ አሰራር መፈጠሩን ገልጿል፡፡

223. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

224. በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት ለናሙና ተረካቢ ብቻ የተመደበ ሰራተኛ አለመኖሩን፣ ስራ ተደርቦ የሚሰራ መሆኑን፣ የናሙና መረከቢያ ሰነድ ያለ ሲሆን ስራ ላይ እየዋለ እንደሆነ እና የተወሰደው ናሙና በተዘጋጀው የባህር መዝገብ እና በኮምፒውተር እንደሚመዘገብ ለማወቅ ተችሏል፡፡

225. በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የናሙና ተረካቢ ባለሞያ የሌለ መሆኑን፣ የናሙና መረከቢያ ሰነድ ግን ያለ መሆኑን፣ የናሙና መረጃዎችም በባህር መዝገብ የሚመዘገቡ ሲሆን ናሙና በማንኛውም ተሸከርካሪ እንዲሁም በማንኛውም ግለሰብ የሚላክ መሆኑን ለመረዳት የተቻለ ሲሆን በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የናሙና ሰራተኛ ባለመኖሩ የኢንስፔክሽን ሰራተኞች በየተራ ናሙና የሚረከቡ መሆኑን፣ የናሙና መረከቢያ ሰነድም አለመኖሩን፣ የናሙናዎች መረጃ ግን በባህር መዝገብ እንደሚመዘገብ ታውቋል፡፡

226. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለቅ/ጽ/ቤቶችና ለተገልጋዮች ማሰራጨቱን በተመለከተ፡-

227. ወቅቱን የጠበቁ መረጃዎች በንግድ ሚ/ር ድህረ-ገፅ ላይ ያሉ ቢሆንም ሚ/ር መ/ቤቱ ወቅቱን የጠበቀ መረጃዎች ለቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ እንደሚልክ እና ቅ/ፅ/ቤቱ ደግሞ መረጃዎችን ለተገልጋዮች የሚልክ ሲሆን ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር ግን ምንም ግኑኝነት የሌላቸው መሆኑን፣ ሚ/ር መ/ቤቱ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ በማሰባሰብ ለቅ/ጽ/ቤታቸው የሚያሰራጭ ሲሆን ቅ/ፅ/ቤቱ ግን በክልል ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር የሥራ ግኑኝነት ስለሌለው መረጃዎችን የማያሰራጩ እና ሚ/ር ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የሚልክ ቢሆንም የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ከባለድርሻ አካላት ጋር ግኑኝነት ስለሌለው ረጃዎችን እንደማያሰራጭ ለማወቅ ተችሏል፡፡

228. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለዉ የሰዉ ሃይል አደረጃጀት የናሙና ተረካቢ ሰራተኛ አደረጃጀት የሌለዉ እንደሆነና የናሙና ተረካቢ ሠራተኛ መቅጥር የማይቻል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

229. ይሁን እንጂ መኒስቴር መ/ቤቱ ናሙናዎችን ያለ ባለሞያ መውሰዱ በሚወሰደው ናሙና ጥራት ላይ እንዲሁም የናሙናው ውጤት አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድር ነው፡፡

***ሁሉንም የሥራ አመራር ያካተተ መደበኛ እና ተከታታይ የማናጅመንት የውይይት መድረክ ያለው መሆኑን በተመለከተ፣***

230. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

231. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁሉንም የሥራ አመራር ያሳተፈ መደበኛ እና ተከታታይ የሆነ የማኔጅመነት /የስራአመራር/ የውይይት መድረክ ፈጥሮ በውይይቱ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በቃለ ጉባኤ እንዲያዙ አለማድረጉ፣

232. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማኔጀመንት ቃለ ጉባኤ አራት ከፍተኛ የሥራ አመራሮችና አንድ የመ/ቤቱ ህዝብ ግንኙነትና የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ በአጠቃላይ አምስት አባላትን የያዘ በመሆኑ ካሉት አስራ ስምንት የማናጅመንት አባላት አንጻር ሁሉንም የከፍተኛ አመራር /የስራ ኃላፊዎች/ ያላካተተ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

233. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁሉንም የሥራ አመራር ያሳተፈ መደበኛ እና ተከታታይ ያለው የማኔጅመነት የውይይት መድረክ ሊኖረው እና በውይይቱ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በቃለ ጉበኤ በመያዝ ተከታታይ ቁጥር ሰጥቶ በአግባቡ ሊይዝ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

234. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር የማኔጅመንት ስብሰባ ላይ የሚነሱትን ነጥቦች በቃለ-ጉባኤ ለመያዝ በ2009 ዓ.ም በእቅድ መያዙን ገልጿል፡፡

235. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

236. የኦዲት ቡድኑ ከቃለ-ጉባኤ መመልከት እንደቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሀምሌ 11/2009 ዓ.ም ጀምሮ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ሁሉንም የሥራ አመራር ያካተተ ሳይሆን የንግድ ሚኒስቴር ሚኒስትሩን፣ የንግድ ማስፋፊያ ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታን፣ የንግድ አሰራርና ሪጉላቶሪ ዘርፍ ሚኒስተር ዴኤታን፣ የሚኒስቴር ፅ/ቤት ዋና ዳይሬክተርን እና የህዝብ ግኑኝነትና ኮሚኒኬሽን ጉዳች ፅ/ቤት ሃላፊን ብቻ ያካተተ መደበኛና እና ተከታታይ የማናጅመንት /የስራ አመራር/ የውይይት መድረክ መኖሩን እና በውይይቱ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን በቃለ ጉበኤ በአግባቡ የተያዙ መሆናቸውን ከቃለ-ጉባኤዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

**በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበር ገምግሞ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን፣ በቅ/ጽ/ቤቶችና በክልሎች በአካል በመገኘት የጋጠሙ ችግሮችን ገምግሞ መፍትሄ የሰጠ መሆኑ በተመለከተ፣**

237. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

238. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክልሎች በማስተባበር በጋራ በቅንጅት መስራት፣ በክልል የሚገኙ ሥነ-ልክ ባለሙያዎች ያለባቸውን የክህሎት ክፍተት ችግር የመሙላት፣ የሚጠቀሙበት ስታንዳርድ የመለኪያ መሳሪያዎች በቂ አለመሆንና አንድ ወጥ አተገባበር እንዲኖር በመገምገም ተገቢውን ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

239. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበርና አሠራር በተሸለና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወን በበቂ ሁኔታ አስፈላጊውን የሆነ ድጋፍ ሊያደርግና አፈጻጸሙን ሊገመግም እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

240. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በክልሎች ህጋዊ ስነ-ልክ አተገባበርና አሰራር ያሉትን ችግሮች በመለየት የክህሎት ክፍተት ለመቅረፍና ስልጠና በመስጠት እንደዚሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶች በመቅረፅ በጀት አስፈቅዶ የትክክለኛ የማረጋገጫ ስታንዳርድ የመለኪያ መሳሪያዎችን በመግዛትና ክልሎችም በጀት በመያዝ ግዢ እንዲፈፅሙ ግንዛቤ በመስጠት ድጋፍ በማድረግ ላይ መሆኑን፣

241. በተጨማሪ በሙያው የሠለጠነ የሰው ሀይል ለማፍራት ካሪኩለም ተቀርፆ የመጀመሪያ ዙር ሰልጣኞች በተግባረ-ዕድ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ስልጠና በመሰጠት ላይ እንደሚገኝ፣ ከቅ/ፅ/ቤቶች የሚቀርቡትን ወርሃዊ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች ላይ በየሩብ ዓመት በመገናኘት ግብረ-መልስ ለመስጠት በ2009 ዓ.ም በእቅድ መያዙን ገልጿል፡፡

242. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

243. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበርና አሠራር የሚገመግም፣ የመፍትሄ ሃሳብ የሚሰጥ እንዲሁም ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን ከደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ቢገለፅም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

**የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያቀርቡትን ወርሀዊ ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን ከገመገመ በኋላ ግብረ መልስ የሰጠ <u>መሆኑን በተመለከተ፣</u>**

244. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

245. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚቀርቡትን ወርሃዊ፤ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመትና አመታዊ ሪፖርቶችን ከገመገመ በኋላ በአፈጻጸም ላይ በሚያጋጥሙና መፍትሄ ሊቀመጥላቸው በሚገቡ ችግሮች ላይ ወቅታዊ የሆነ ግብረ መልስ አለመስጠቱ ተገኝቶ ነበር፡፡

246. በቅ/ጽ/ቤቶች የሚሠሩ የገቢና ወጪ ዕቃዎች ከሀገር ሲወጡና ወደ ሀገር ሲገቡ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ እና የሥነ ልክ የቁጥጥርና የክትትል ሥራ እንዲሠሩ በውክልና ለክልል ንግድ ቢሮዎች በሠጠው መሠረት ሥራው በተፈለገው ሁኔታ እንዲሠራ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በክልል ንግድ ቢሮዎች በአካል በመገኘት በገቢና ወጪ ዕቃዎች እና በህጋዊ ስነልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ የተከናወኑትንና በክንውን ወቅት የገጠሙ ችግሮችን ፣በማየት ለችግሮቹ የመፍትሔ እርምጃ በመስጠት በተሟላ መልኩ ሊገመግም

247. እንዲሁም ቅ/ጽ//ቤቶች ለሚያቀርቧቸው ወርሀዊ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ የአፈፃፀም እና 1ለ5 ሪፖርት ከገመገመ በኋላ ግብረ መልስ በመስጠት በሪፖርታቸው የተመለከቱትን የሥራ ክፍተቶች የሚደፍኑበት የሚያስችል የመፍትሔ እርምጃ ሊሰጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

248. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 01.108/6135 ነሀሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በክልሎች ህጋዊ ስነ-ልክ አተገባበርና አሰራር ያሉትን ችግሮች በመለየት የክህሎት ክፍተት ለመቅረፍና ስልጠና በመስጠት እንደዚሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶች በመቅረፅ

በጀት አስፈቅዶ የትክክለኛ የማረጋገጫ ስታንዳርድ የመለኪያ መሳሪያዎችን በመግዛትና ክልሎችም በጀት በመያዝ ግዢ እንዲፈፅሙ ግንዛቤ በመስጠት ድጋፍ በማድረግ ላይ መሆኑን፣

249. በተጨማሪ በሙያው የሠለጠነ የሰው ሀይል ለማፍራት ካሪኩለም ተቀርፆ የመጀመሪያ ዙር ሰልጣኞች በተግባረ-ዕድ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ስልጠና በመሰጠት ላይ እንደሚገኝ፣ ከቅ/ፅ/ቤቶች የሚቀርቡትን ወርሃዊ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች ላይ በየሩብ ዓመት በመገናኘት ግብረ-መልስ ለመስጠት በ2009 ዓ.ም በእቅድ መያዙን ገልጿል፡፡

250. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

251. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቅ/ጽ/ቤቶችና በክልሎች በገቢና ወጪ ዕቃዎችና በህጋዊ ስነ ልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ በአካል በመገኘት የተከናወኑትንና በክንውን ወቅት የጋጠሙ ችግሮችን በማየትና የሚገመግምና ላጋጠሙ ችግሮች መፍትሔ የሚሰጥ መሆኑን በንግድ ሚኒስቴር የሞጆ ተወካይ ቅ/ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

252. የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቅ/ጽ/ቤታቸው በገቢና ወጪ ዕቃዎችና በህጋዊ ስነ ልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ በአካል በመገኘት የተከናወኑትንና በክንውን ወቅት የጋጠሙ ችግሮችን በማየትና የሚገመግም እና መፍትሔ የሚሰጥ ቢሆንም ግብረ-መልስ በፅሁፍ የማይሰጥ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

253. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት በገቢና ወጪ ዕቃዎችና በህጋዊ ስነ ልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ በአካል በመገኘት የተከናወኑትንና በክንውን ወቅት የጋጠሙ ችግሮችን በማየትና የሚገመግም መሆኑን የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ቢገልፁም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

254. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያቀርቡትን ወርሀዊ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን ከገመገመ በኋላ ግብረ መልስ መስጠቱን በተመለከተ፡-

255. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሞጆ ፣ የአዳማ እና የሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያቀርቡትን ወርሀዊ ፣ የሩብ ዓመት ፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን የሚገመግም ቢሆንም ከገመገመ በኋላ ግብረ-መልስ በፅሁፍ የማይሰጥ መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

256. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና የህጋዊ ሥነ-ልክ ደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን ብቃትና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

### 3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና በህጋዊ የመለኪያ መሳሪያዎች ደረጃ ፍተሻ እስትራቴጂክ ዕቅድ ፣ ስትራቴጂክ ዕቅዱን መሰረት አድረጎ አመታዊ ዕቅድ ያዘጋጀ እና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የእቅድ ክንውን ሪፖርት የሚያቀርብ መሆኑን፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው እንዲሁም የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት እንዲወጡ የማያደርግበት ሁኔታ መኖሩን፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት እና የጊዜያዊ መልቀቂያ አሰራር እንዲቀር ማድረጉ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አንዳንድ ተገልጋዮች የተሸጋጋሪ ሚዛን (Standard Weight) የክብደት ማነፃፀሪያዎች ቬሪፋይ ለማስደረግ የማነጻጸሪያ መሳሪያዎችን ውል በማስገባት የሚያውስ መሆኑ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተፈላጊውን የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርት የማያሟሉ ምርቶችና ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በትብብር የሚሰራ መሆኑ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መደበኛ እና ተከታታይ የማኔጅመነት /የስራአመራር/ መድረክ ፈጥሮ በውይይቱ በማድረግ በውይይቱ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን በቃለ ጉባኤ እንዲያዙ የሚያደርግ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

## 3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በገቢና ወጪ ዕቃዎች እና በህጋዊ መለኪያ መሳሪያዎች ደረጃ ፍተሻ አፈጻጸም ዕቅድ ክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች በመለየት የመፍትሄ እርምጃ አለመውሰዱ ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የአሠራር መመሪያው ሊሻሻል እንደሚገባው ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያከናውናቸው የደረጃዎች ፍተሻ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን በሥሩ የሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች በተሟላ ሰው ኃይል በማደራጀትና ለሥራው የሚያስፈልጉ አስፈላጊ ግብዓቶችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን እየተከታተለና እየተቆጣጠረ አለመሆኑ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱአንዳንድ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ናሙና ተወስዶ የደረጃ ፍተሻ ተፈትሾ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በሚያዘው መሠረት ደረጃቸው ሳይረጋገጥ በጊዜያዊ መልቀቂያ እንዲለቀቁ የሚያደርግ መሆኑን፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ እንዲያግድ በተሰጠው ስልጣን ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች በተስማሚነት ምዘና በላብራቶሪ ፍተሽ ተደርጎላቸው ከደረጃ በታች የሆኑት እንዲታገዱ አለማድረጉን እና መስፈርት የማያሟሉትን በመቆጣጠር ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ አለመውሰዱ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞች የላብራቶሪ ፍተሸ ውጤት በደንበኞች ላይ ቅሬታ እንዳያሳድር በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያሳውቅ አስፈላጊውን ክትተልና ቁጥጥር ያላደረገና በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በሚያዘው መሰረት የሚወሰዱ ናሙናዎች ከውጫዊ ተጽኖ ነጻ ሆነው የጥራት ባህሪያቸው ሳይለወጥ ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ውስጥ ለላብራቶሪ ምርመራ ቶሎ እንዲቀርቡ ያለመደረጉ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት በተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊ ማድረጋቸው ተገቢውን ቁጥጥር ያላደረገና የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ሥራዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናክረው መስራታቸውን ለማረጋገጥ በቂ የሆነ ስታንዳርድ የመለኪያ መሣሪያዎች የሌሉት መሆኑ ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክልሎች ላይ የሚገኙ የሕጋዊ ሥነ-ልክ ባለሙያዎች የክህሎት ክፍተት ያለባቸውና የሚጠቀሙበት ስታንዳርድ ለመለኪያ መሳሪያዎቹ ለጉዳዩ ትኩረት ካለመስጠትና ከየአቅም ውስንነት አኳያ በየጊዜው ካሊቤሬት የማይደረግና ስራዎቹ መሰራታቸውን የሚከታተልበትና ክፍተቶችና ጥንካሬዎችን የሚከታተልበት አሰራር የሌለው መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ ቬርፊኬሽን ክፍያ በ1966 ዓ.ም የወጣ ሲሆን አሁን ከሚሠጠው አገልግሎትና ወጪ አንጻር ክፍያው ወቅታዊና ተመጣጣኝ ከጊዜው አንጻር እንዲሆን ማሻሻያ ወይም ማስተካከያ ያለመደረጉ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአስፈጻሚ መ/ቤቶች ፣ቅ/ጽ/ቤቶች፣ በክልሎችና ባለድርሻ አካላት የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተጠናከረ መልኩ በቅንጅት እንዲሰሩ ከተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት በአፈጻጸም ላይ በሚያጋጥሙ ችግሮችና ሊወሰዱ በሚገባቸው የመፍትሄ እርምጃዎች ላይ የሚወያይ መደበኛ የሆነ ጉባኤ በመጥራት ውይይት የማያደርግ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች የሚካሄዱ የህጋዊ ስነ ልክን የስራ አፈጻጸምን በየሩብ ዓመቱ ውይይት ለማድረግና በየስድስት ወሩ ግምገማ ለማድረግ ዕቅድ ቢያዘጋጅም በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ያለማድረጉ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት መዘግየት ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር በመሆን ችግሮችን እንዲቀረፉ ተከታታይነት ያለው ውይይት በማድረግ ለችግሮቹ መፍትሄ እንዲቀመጥ ያለማድረጉ፣
- በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች የናሙና ተረካቢ ሠራተኛ ባለመኖሩ ናሙናዎች በናሙና መረካከቢያ ሰነድና በመረጃ ቋት እንዲያዙ ያልተደረጉ፣ ለቅ/ጽ/ቤቶች ለስራ አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል የአሰራር ልዩነት እንዳይፈጠር ወጥ በሆነ መልኩ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃዎችን በሚፈለገው ደረጃ በማሰብሰብና

በማደራጀት እንዲሰራጩ አለመደረጉ፣ እንዲሁም ከተስማሚነት ምዘና ድረጅት ጋር መረጃ በመለዋወጥ ወርሃዊ ወይም የሩብ አመት ሪፖርት በጋራ ገምግሞ የማያውቅ መሆኑ፣

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መደበኛ እና ተከታታይ የማኔጅመነት /የስራአመራር/ መድረክ ፈጥሮ በውይይቱ በማድረግ በውይይቱ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን በቃለ ጉባኤ እንዲያዙ የሚያደርግ ቢሆንም ውይይቱ ሁሉንም የሥራ አመራር ያላሳተፈ መሆኑ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበርና አሠራርን ላይ ያሉትን ችግሮችን በሰው ኃይል ስልጠና፣ በመሳሪያዎችና ሌሎች አስፈላጊ በሆኑ ድጋፎች በመለየት እየገመገመ በበቂ ሁኔታ ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቅ/ጽ/ቤቶችና በክልሎች በገቢና ወጪ ዕቃዎችና በህጋዊ ስነ ልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሚያቀርቡ ወርሀዊ ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን እየገመገመ ግብረ መልስ የማይሰጥ መሆኑ፣

እስከአሁን መኖሩ ታውቋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

257. በመጀመሪያው የክዋኔ ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑት የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡

258. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ባልተስተካከሉና የእርምት እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት የንግድ ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት፣ የንግድ ሚኒስቴር ቅርንጫ ፅ/ቤቶች ፣ የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች፣ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡